# ክፍል ፪



# ምዕራፍ ፲፯

# የኢትዮጵያ መንግስት ሁኔታና የለውጥ አዝማሚያ

## ዘውዳዊው ስርዓት

*ኬዳም በልዩ ልዩ ቦታዎች እያገለገሉ በአብዛኛው ገጠራማ በሆነችው ኢትዮጵያ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ ሕዝቦችን በወንጌል እየደረሱ የወጣትነት ዕድሜአቸውን አጠናቅቀው ወደ ጉልምስና ተሻገሩ። በዚህ የጉልምስና ዘመናቸውም በዚያ ዘመን አጠራር በተወሰኑ የአገሪቱ ጠቅላይ ግዛቶች የተገደበ አገልግሎታቸው ብሔራዊ ገጽታ እያገኘ መሄድ ጀመረ። በመላ አገሪቱ የሚገኙ ቤተ ክርስቲያናት ከቋሚ የአገልግሎት ስፍራቸው ባሻገር በመነሳት እየተዘዋወሩ አስደናቂውን ወንጌል በልዩ ጸጋ የሚያስተምሩትንና የሚሰብኩትን ኬዳምን እየጋበዙ ይገለገሉ ጀመር።*

*የአገሪቱ መዲና የሆነችው እና ወንጌል በልዩ ልዩ የሚሲዮን ተቋማት አማካኝነት የተሰበከባት፣ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ በርካታ የውጪም ሆነ አገር በቀል ቤተ ክርስቲያናት የተተከሉባት አዲስ አበባም የእኚን ወንጌላዊ ዝና ሰምታ በተለያየ አጋጣሚ እየጠራች ትጠቀምባቸው ጀመር። ኬዳም በተለያዩ ክረምቶች ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በዚህች ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ ቆዩ፤ በኋላም ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ኬዳምን በቋሚነት እንዲገለግሏት ፈለገች።*

*በዚሁ ጊዜ አዲስ አበባ በፈጣን እድገት ላይ የነበረች የበርካታ አገራት ቆንስላዎች፣ የንግድ ሰዎች እና ኢንቬስተሮች የሞሉባት ዓለም ያፈራችው ዘመን አመጣሽ የዕድገት መገለጫ የሆነች በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካም ካሉ አዳጊ ከተሞች አንዷ ነበረች። አዲስ አበባ በዚህ ብቻ ሳታበቃም ዘመን አመጣሽ ርዕዮተ ዓለሞች (የሦስት ሺህ ዘመን ነው የሚባለውን ዘውዳዊ ሥርዓት ሳይቀር መነቅነቅ የጀመሩበት፤) ከታህሳስ 1953 የጀኔራል መንግስቱ ነዋይ መፈንቅለ መንግስት ሙከራ በኋላም የንጉሡም ዙፋን የሚደፈር መሆኑ ታይቶ አዳዲስ ሃሳቦች በየሰዉ ልብ የገቡበት፣ ከተማይቱም የእነዚህ አስተሳሰቦችና የለውጥ ትልሞች መፈልፈያ እና መናኸሪያ የሆነችበት ጊዜ ነበር።*

ነልዩነት እና የታዳጊነት ዕድሜያቸውን በዘመናዊ ትምህርት ሳይሆን በእረኝነት እና በግብርና ያሳለፉትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በወንጌል ካመኑ በኋላ የፊደል ገበታን "ሀ" ብለው የቆጠሩት፣ የጽሕፈትንም ሆነ የንባብ ትምህርትን መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተው ያጠናቀቁት ኬዳሞ ዘመናዊቱ አዲስ አበባ ስትጠራቸው "እችለዋለሁ ወይ?" የሚል ጥያቄ ተፈጥሮባቸው ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ያኔ የጌኛ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን የሚመሩት እና በልዩ ልዩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በኃላፊነት የሚሠሩት እነ አቶ ጥላሁን ኃይሌ፣ አቶ ማሞ ገ/መስቀል፣ አቶ ሽፈራው ወ/ሚካኤልና አቶ ብርሃኑ ደረሰን የመሳሰሉ የተማሩ ሰዎችን እንዲያገለግሉ መፈለጉ ለኬዳሞ ነገሩን ከባድ የሚያስመስልባቸው አጋጣሚ ነበር።

ይሁንና አዲስ አበባም ሆነች የዚያ ዘመኗ ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ ለኬዳሞም ሆነ ለሌሎች ኢትዮጵያውያን ከዚህም በላይ አሳሳቢ እየሆነ የሄደበት ጊዜ መሆኑም በግልጽ ይታይ ነበር። ኬዳሞ በእርግጥ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እየተዘዋወሩ እንዳገለገሉ እና በሕዝቡ መካከል እየተዘዋወረ የሕዝቡን የልብ ትርታ እንዳደመጠ ሰው የአገሪቱን ሁኔታ በአንክሮ እየተከታተሉ ይመረምሩ እና ይጸልዩ ነበር። በተለይም እርሳቸው በዘመዶቻቸው ተወክለው በግፍ ስለተወሰደ መሬት አዲስ አበባ ድረስ እየተመላለሱ በተሟገቱበት ጊዜ በየአካባቢው ያለውንም የሕዝብ ጩኸት እና እምባ በማየት ገና ጉምጉምታው ካልበረታበት 1956 ዓ.ም ጀምሮ ታላቅ የምልጃ ጸሎት ስለ አገራቸው እና ስለ ሕዝቡ ይጸልዩ ነበር። በዚህ ጊዜ ያደረባቸው ታላቅ የጸሎት ሸክምም በኢትዮጵያ ምድር ደም መፋሰስ ሳይኖር የሚበደለው ሕዝብ ሁሉ በእኩልነት የሚታይበት ሥርዓት እንዲመጣ ፍትሕ እንዲሰፍን ነበር። ኬዳሞ አገር ለአገር ዞረው ሲያገለግሉ ሕዝብ በባላባቶች ያለ አግባብ ሲበደል እና ተሳቅቆ ሲኖር አይተዋል። በብዙ አካባቢዎች ክርስቲያኖች የጸሎት ቤት መሥራት ተከልክለው ሲንገላቱ ተመልክተዋል። ሰዎች ከነ ዘር ማንዘራቸው ሲኖሩበት በነበረ ምድራቸው እንደ አዲስ እንግዳ መቀበሪያ አጥተውና አርሰው እንዳይበሉም ተከልክለው ሲሰቃዩም ታዝበዋል።

ከዚህም በላይ በገዛ ላባቸው ባፈሩት ኃብት የገዙት ጥሩ በቅሎ ላይ ተቀምጠው መሄድ እንኳ ሲከለከሉ እያዩ የሕዝቡንም የከፋ ምሬት እና ጉርምርምታ እያደመጡ ነገሩን በእግዚአብሔር ፊት ከማቅረብ በስተቀር አማራጭ ስላልነበረ በትጋት ወደ እግዚአብሔር ሲያቀርቡ የሕዝቡም ጉርምርምታ እና ምሬት እየበዛ ሲሄድ ሀሊናቸውን ጨምድዶ ያዘው። የነበረው ኋላ ቀር ሥርዓት በሕዝቡ ላይ የጫነውን የመከራ ቀንበር ገና በወንጌል አምነው ስደት ሲደርስባቸውና በጌዴኦ ምድር ስለ ወንጌል ዋጋ በከፈሉበት ወቅት ነበር ያዩት። ኬዳሞ ከ1956 ዓ.ም በፊት የነበረውን ሁኔታ ሲያስቡ በተለይ አንድ ገጠመኛቸውን እንደ ትልቅ ማስረጃ ሁል ጊዜ ያስታውሱታል። ነገሩ የተከሰተው በ1952 ዓ.ም በሻሾንዋ የእሸጎላ መንደር በማገልገል ላይ ሳሉ ነበር። በወቅቱ የወንጌል አዝመራው ይዞላቸው ብዙዎች የምሥራቹን ቃል ሰምተው ቅዱስ ቃሉን ተጠምተው እየተሰበሰቡ መማር የጀመሩበት ወቅት ነበር።

አንድ ዕለትም እንደተለመደው ብዙዎች ተሰብስበው መጽሐፍ ቅዱስ እየተማሩ ሳለ አንድ የባላባት ሹም ድንገት ከተፍ ይላል። በጊዜው ብዙዎች ባላባቱ የግሉን እርሻ እያሠራቸው ቃሉን ለመማር ሲሉ ተደብቀው መጥተው ስለነበር ሹሙን ሲያዩ ደነገጡ። እንደፈሩትም ሹሙ የባላባቱን ሥራ ትተው መጽሐፍ ቅዱስ የሚያጠኑትን ትልልቅ ሰዎች ልክ እንደ ትንሽ ልጅ በዱላ እየደበደበ ሥራ ወደ ሚሠራበት እርሻ ይዟቸው ሄደ። በዚህ ጊዜ "ምላሜ" የሚባል ልጅ ያለውና በልጁ ስም "አበ ምላሜ" እየተባለ የሚጠራ አንድ ትልቅ ሰው በደረሰበት ግፍ ከፉኛ ተማርሮ ሹሙ እና እነ ኬዳሞ ባሉበት በሰው ሁሉ ፊት እጁን ወደ ሰማይ ዘርግቶ "እግዚአብሔር ሆይ፦ አንተ ንጉሥ አይደለህምን? ይህንን አታይምን?" በማለት በታላቅ ድምፅ ጮኸ። በጊዜው ሰው ሁሉ በድንጋጤ ያየው ነበር። ነገር ግን ወደ ላይ የጮኸው ጩኸት ከወንጀል ተቆጥሮም ሹሙ እየደበደበ ይዞት ወደ ባላባቱ እርሻ ሄደ።

ኬዳሞ ዛሬም ድረስ አበ ምላሜ እንደ መብረቅ ባለ ኃይለኛ ድምፅ የጮኸውን ጩኸት ያስታውሳሉ። ወደላይ የተዘረገት እነዚያ የጭቁን ኢትዮጵያዊ ገበሬ እጆችም ሁል ጊዜ ከእዝነ ልቦናቸው አይጠፉም። ከዚህም የተነሣ ያ በሻሸን ተራሮች አስተጋብቶ ወደ መላው ኢትዮጵያ ክፍላተ አገራት የተሸጋገረ ጩኸት ከዓመታት በኋላ በኢትዮጵያ ታላቅ ለውጥ እንዳመጣ ያምናሉ። ስለሆነም ኬዳሞ ሁል ጊዜ ሲጸልዩ የማይቀረው ለውጥ ያለ ደም መፋሰስ እና ጦርነት እንዲሆን ይማልዱ ነበር። ከ1956 ዓ.ም ሐምሌ ወር ጀምሮም የአገሪቱ መሬት የሕዝብ እንዲሆን በብርቱ መጸለይ ቀጠሉ።

ይህ በአገሪቱ ተንሰራፍቶ የነበረ የገዢዎች እና የየአካባቢው ሹማምንት ለሕዝቡ እንደ መርግ የከበደ በደል የሕዝብ አካል ለሆኑት ኬዳሞም የድርሻቸውን ያህል ደርሶባቸዋል። የመጀመሪያው በደል በሻሸን የሙሉ ጊዜ አገልግሎታቸውን አቁመው የራሳቸውን ሥራ እየሠሩ እናታቸውን እየደገፉ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ሲሆን የባለቤታቸውን የእንጀራ አባት መሬት ለመውሰድ አንዱ ጉልበተኛ የኔ ነው ብሎ ከሰሳቸው። በዘመኑ ፍርድ የሚሰጠው ጉቦ እየተበላ ስለነበር ለሰውየው ተፈረደለት። ኬዳሞ ከዚያ ዘመን አንጻር የተሻለ ትምህርት እና እውቀት ስለነበራቸውም አዲስ አበባ ድረስ ሄደው እንዲከራከሩ ተወክለው ለወራት ተመላልሰው ተሟግተው ሙግታቸው በሽንፈት ተደመደመ። ይሄኛ መሬቱ የራሳቸውም ባይሆን የዓይን ምስክር ሆነው በደልን እና የተዛባ ፍርድን ተቀበሉ። በዚህ ጊዜም ወደ እግዚአብሔር ከመጮህ ውጪ ምንም አማራጭ አልነበራቸውም እና ስለ ፍትህ ይጮሁ ጀመር።

በሌላ ጊዜ ደግሞ በቢቾ ማዕከል የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በምክትል ርዕሰ መምህርነት እየሠሩ ብዙ ተደራራቢ ኃላፊነቶች ተሸክመው በሚያገለግሉበት ዘመን አንድ አጋጣሚ ተፈጠረ። በ1960 ዓ.ም ሆሳዕና ከተማ የልጅ አበበ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከፍቶ ታላቅ የምረቃ በዓል ተካሂዶ ነበር። በዚሁ ጊዜም ኬዳሞ እና ቢቾ የሚኖሩ ሚስዮናውያን በበዓሉ ላይ ለመታደም በሄዱበት ወቅት የክብር እንግዶችን በመቀበል የሚያስተናግዱ አስተናባሪዎች ሚስዮናውያኑን ተቀብለው የክብር

ስፍራ ከሰጡ በኋላ ኬዳሞን ግን ወደ ጎን ገፍተው ገለል አደረጓቸው። በዚህ ጊዜ የደረሰባቸው አድልዖ እና ማግለል ክፉኛ ያበሳጫቸው ኬዳሞ በታላቅ ቁጣ በተሰበሰበ አድምተኛ ፊት "ይህ አድልዖ እንዲጠፋ ... ይህ ልዩነት እንዲወገድ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ ወንድ ሴት ሳይባል ወታደር መሆን አለበት።" ብለው በጩኸት ተናገሩ። በዚህ ጊዜ የሥነ ሥርዓቱ አስተናባሪዎች ተደናግጠው እየተርበተበቱ እርሳቸውንም ጥሩ ቦታ እንዲቀመጡ አደረጓቸው። እነዚህን በመሳሰሉት ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፋቸውም ኬዳሞ የለውጥ ሽታ እንዲሸታቸው እና ወደ ፊት ስለሚመጣው የለውጥ ሂደት እንዲጸልዩ አደረጋቸው። በዚሁ መኃልም ከአዲስ አበባዋ የያኔዋ መሠረተ ሕይወት የዛሬዋ ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አገልግለኝ የሚል ጥሪ መጣላቸው።

ምንም እንኳን ወቅቱ አዲስ አበባን የሚያስመኝ ባይሆንም እግዚአብሔር ግን ወንጌላዊውን በዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ ወደ አዲስ አበባ ሊወስዳቸው ስለፈለገ በግልጽ ኖህን መርከብ እንዲሠራ እንዳዘዘው፤ አብርሃምን ከዘርህ ከነገድህ ተለይተህ ውጣ እንዳለው፤ ኤልያስን ቁራ እንዲመግብህ አዝዣለሁ ብሎ ወደ ኮራት ፈፋ እንደላከው፤ ኬዳሞንም "አንተም ታዘዘኝ" የሚለውን ድምፅ ሰምተው ወደ አዲስ አበባ አመሩ። የአገሪቱ የለውጥ ሁኔታም ከድጡ ወደ ማጡ ሲገባ፤ ስለ ወንጌል ከቀደመው በከፋ እና በብዙ እጥፍ ዋጋ ሊከፈል፤ ብዙ ኢትዮጵያውያን ሊሞቱ፤ ብዙ ወጣቶች ሊገደሉ፤ ብዙዎችም በመከራ ውስጥ የሚያልፉበት ጨለማ ዘመን እየመጣ ነበር። ኬዳሞም ያንን በቅርበት እንዲታዘቡ በተለይ የመከራው እና የደም መፋሰሱ መነሻ የክህደቱ እና የአዋጁ ምንጭ ወደሆነችው አዲስ አበባ አምርተው የአይን እማኝ እንዲሆኑ በአስፈሪ ሁኔታ ውስጥ አልፈውም ለብዙዎች ጽንቶ መቆም ምክንያት እንዲሆኑ ከገጠር አገልጋይነት ወደ ከተማ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ መሪነት ተሻገሩ። የአዲስ አበባ መጻኢ አስከፊ ሁኔታም ወዲያውኑ ይገለጥ ጀመር።

## የመጨረሻው የዘውድ በዓል

ጊዜው 1966 ዓ.ም ዕለቱ ደግሞ ጥቅምት 23 ነበር። ይህች ዕለት በቀድሞው ዘውዳዊ አገዛዝ ዘመን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘውድ የደፉባትና ያም ቀን በመላ ሀገሪቱ በብሔራዊ ደረጃ ተከብሮ የሚውልባት የበዓል ቀን ነበረች። ወቅቱ እዚህም እዚያም ተማሪዎች፣ ሠራተኞች ብሎም በየገጠሩ የሚገኙ የአገሪቱ የጀርባ አጥንት የሆኑ ገበሬዎች ተቃውሞ የሚያሰሙበት ውጥረት የነገሰበት ዓመት ነበር። በወቅቱ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ፊውዳላዊ መንግስት ከዘመናዊው የዓለም ሁኔታ ጋር አብሮ መሄድ አቅቶት ለመውደቅ አፋፍ ደርሷል።

ወንጌላዊ ኬዳሞ የአገሪቱን እና የንጉሡን ሁኔታ ሲያዩ ትልቅ ሐዘኔታ ይሰማቸው ነበር። በኬዳሞ እምነት ኃይለ ሥላሴ ትምህርት በመላ አገሪቱ እንዲስፋፋና ሰው ሁሉ እንዲማር የሚፈልጉ መሪ ነበሩ። ንጉሡ በሃይማኖት እኩልነት የሚያምኑ እና ተግባራዊ እንዲሆን በግላቸው የሚጥሩ ቢሆኑም ከንጉሡ ሥር የነበሩ በመላ አገሪቱ

ያለውን ሕዝብ የሚገዙ መሳፍንት፣ መኳንንት እና የየአገሩ ባለባቶች ሁሉን ስለያዙ ንጉሡ አቅም አጥተው ነበር። በዚያ ዘመን ተዘዋውሮ የአገሪቱን ሁኔታ ያየ ሰው በቀላሉ እንደሚረዳው በጊዜው በመላ አገሪቱ የግፍ አገዛዝ ሰፍኖ ነበር። ንጉሡ በዚሁ ጉዳይ ዙሪያ ተጠይቀው ሲመልሱ "አንድ እጅ አያጨበጭብም፤ እኔ አንድ እጅ ነኝ" ብለዋል ሲባል መስማታቸውን ኬዳሞ ያስታውሳሉ። በኬዳሞም እምነት ንጉሡ የቱንም ያህል መልካም አሳቢ የነበሩ ቢሆኑም የበታቶቻቸው ካልተባበሩ ብቻቸውን ምንም ሊሠሩ አይችሉም ነበር። ንጉሡ መኳንንቶቻቸውን ተቃውመው ለመነሳት እንኳን የሚይዙት የላቸውም ነበር። የእርሳቸው ሥልጣን የቆመው በሕዝቡ ሳይሆን በመኳንንቱ ነበርና። ንጉሡ ሕዝቡን እንኳን ልያዝ ቢሉ ያን ጊዜ ሕዝቡ አቅም አልነበረውም።

ከዚህም ባሻገር ንጉሥ የዕድሜ ዘመናቸውን በሙሉ አገሪቱን ሲመሩ ኖረው እርጅና ተጫጭኗቸዋል። ስለሆነም በ1966ቱ የንግሥ በዓል ኬዳሞ ወደ አዲስ አበባ መጥተው የመናገሻ ከተማዋ ኗሪነታቸው ብዙም ያልቆየ ቢሆንም የዚህን ዓመት የንግሥ በዓል በላቀ ጉጉት ሊታደሙበት ወሰኑ። ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ታደለች ጋርም በደንብ ተዘጋጅተው በአገሪቱ ፓርላማ ግቢ ንጉሡ የሚያደርጉትን የበዓል ንግግር ለማድመጥ በጊዜ ወደ ግቢው አቀኑ። በንጉሣዊው ሥርዓት መሠረት ንጉሡ ለመሳለም እና የቅዳሴ ሥርዓት ለመካፈል አስቀድመው ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በክብር አጀብ ሄዱ። ኬዳሞ እና ባለቤታቸውም በዚሁ አጋጣሚ በዋናው መንገድ የሚኖረው አጀብ እንዳያስቸግራቸው በአቋራጭ አድርገው ወደ አገሪቱ ፓርላማ መገኛ ቀድመው ደረሱ። በፓርላማው ግቢ ሆነውም የንጉሡን መመለስ እና የሚያደርጉትን ንግግር በጉጉት የተጠባበቁበት ምክንያት ያ ንግግር በአገሪቱ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣ በማመን ነበር። በዚያ ዕለት 80 ዓመት የሞላቸው ንጉሥ ሥልጣናቸውን ለሌላ ተተኪ እንደሚያስረክቡ እንዲሁም በየቦታው የሕዝብ ሮሮ የበረታበትን የመሬት ጉዳይ ምላሽ እንደሚሰጡ እና የሕዝቡ እንደሚያደርጉ ኬዳሞ እርግጠኛ ሆነው ይጠባበቁ ነበር።

በዕለቱ ንጉሡ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በተለመደው ታላቅ አጀብ በክብር ተመለሱና ኬዳሞ የጠበቁትን ንግግር አደረጉ። ይሁንና የንግግራቸው ይዘት ወንጌላዊው ያሰቡት ሳይሆን በተቃራኒው ነበር። ንጉሡ በእርጅና በተዳከመ ድምጻቸው "አገራችንንና ሕዝባችንን በሕይወት ባለንበት ዘመን ሁሉ እንመራለን።" አሉ። በዚህ ጊዜ ኬዳሞ እጅግ ተበሳጭተው አጠገባቸው ወደነበረችው ባለቤታቸው ዞር በማለት "ኩማንች ሾሌአኮን ዲለከሞዬ ሞዕሎቶ ጀሪሳ ሾሌ አኪቴ ዲለኮሞኪ አንኤገሮሞክ ከበል ኢስቤዮን ኢስአሊክ መቶ፤ አፉሊከሚሳ ኢቶጴ ኡለም አቡሳኒን ኡወከሚሳ ..." በማለት ተናገሩ። የተናገሩት ነገር ትርጓሜም "ታደለች፤ እኚህ ሰው ሳይዋረዱ ከስልጣን እንደማይወርዱ ታያለሽ። ተዋርደው ይለቃሉ፤ እኔ ዛሬ ጠብቄ የነበረው ሥልጣን ለልጃቸው አስረክበው እርሳቸው እንደሚያርፉ እና መሬት ለገበሬው እንዲመለስ እንደሚያደርጉ ነበር። ..." ማለታቸው ነበር። ኬዳሞ በጊዜው በሃዲይኛ የተናገሩት አጠገባቸው ያሉ ሰዎች እንዳይሰሟቸው ነበር።

ይህ የዘውድ በዓል ሲከናወን ሥርዓቱ ጊዜ ወስዶ ሰዓቱ 6:30 ሆኖ ነበር። ኬዳሞም የንጉሡን ተስፋ አስቆራጭ ንግግር ከሰሙ በኋላ በዚያ ለመቆየት ምንም ትዕግስት ስላልነበራቸው ወዲያው በሕዝብ መሃል አቋራርጠው ወጥተው ከመንገዱ መጨናነቅ የተነሳ ወደ ቤት መሄድ ስላልቻሉ በአቅራቢያቸው ወዳገኙት አንድ ምግብ ቤት ገብተው እንደ ዛሬ ዘመን የተዘጋጀውን መብላት ሳይሆን እንዲዘጋጅ ጠይቀው ምሳቸውን ተመገቡ። ቡና አስፈልተውም ጠጡ።

የኬዳሞ ትንቢታዊ ንግግር ወዲያው በተከታታይ ይፈጸም ጀመረ። የካቲት ወር ላይ ተማሪዎች "መሬት ላራሹ" ብለው ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ አደረጉ። ተከታታይ ለውጦችም በመምጣታቸው ንጉሡም በወታደራዊ ደርግ ከሥልጣን ተነሱ። የጥቅምት 23 የዘውድ በዓልም ከዚያች ዕለት በኋላ በአገሪቱ ዳግመኛ አልተከበረም።

በእነዚሁ ጊዜያት ሁሉ ኬዳሞ ምንም በንጉሡ ሥልጣን መውደድ ቢያዝኑም ሁል ጊዜ ይጸልዩላቸውና ብዙ ጊዜም በእምባ ስለ ጃንሆይ ለእግዚአብሔር ያሳስቡ ነበር። ንጉሡን ከሥልጣን ያስወገደው ደርግም የንጉሡን ሁኔታ ለተወሰኑ ጊዜያት ሸፋፍኖ አቆይቶት ነበር። አንድ ዕለት ኬዳሞ በአውቶብስ ውስጥ እየተጓዙ እያለ የአውቶብሱ ሬድዮ የንጉሁን መሞት አወጀ። ኬዳሞም ፍጻሜያቸው ስላላማረው ንጉሥ ከልብ አዝነው አምርረው አለቀሱ።

## በእሳት ውስጥ መንገድ አለው!

በእሳት ውስጥ መንገድ አለው፣

በማዕበል መንገድ አለው፣

በወጀብ መንገድ አለው፣

ታዲያ ምን ያሰጋኛል ለምን እታወካለሁ፣

ኢየሱስ መንገዴ ነው በድል እራመዳለሁ።

ይህ መዝሙር የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን "ሀ" መዘምራን የዘመሩትና በአስፈሪው ዘመን፣ በችግር ጊዜ፣ በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር መንገድ እንዳለው የሚናገር መዝሙር ነው። እኔም ወደ አዲስ አበባ ከመጣሁ በኋላ በግሌ እንዴት ባለ ሁኔታ ውስጥ እያለፍኩ ሳገለግል እንደነበር በእውነትም እግዚአብሔር በእሳት ውስጥ መንገድ እንዳለው በሕይወቴ ያየሁትን ልተርክላችሁ።

የአዲስ አበባዋ አንጋፋ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እና አንጋፋዎቹ በመላው ቃለ ሕይወት የታወቁና የተከበሩ መሪዎቿ ያደረጉልኝን ጥሪ ተቀብዬ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑንም አውቄ በ1965 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ አመራሁ። ብዙ ወዳጅ ዘመዶቼ እንደመከሩኝ አብዛኛውን የአገልግሎት ዘመኑን በገጠራማው የአገሪቱ ክፍል ላሳለፈ እና በአንጻራዊነት ኑሮ በጣም ከሚረክስበት ስፍራ ተነስቶ ወደ አዲስ አበባ መግባት

ለእንደኔ አይነቱ ሰው ከባድ ውሳኔ ነበረ። በተለይም ሰባት ልጆች ላለው ሰፊ ቤተሰብ መኖሪያ ቤት ማግኘትም ሆነ የቀለብ ነገር ፈታኝ እንደሚሆን ጥርጥር አልነበረውም።

እኔና ቤተሰቤ ግን በ1966 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ስንመጣ በጣም ስጋት የሆነብኝ በእኛም ሆነ በሰው ዘንድ ሲታሰብበት የነበረው የኑሮ ሁኔታ አልነበረም። ለእንደኔ ዓይነቱ ለብዙ ዓመታት በ10 ብር የቀለብ ክፍያ ቤተሰብ ይዞ ሲያገለግል ለኖረ ወንጌላዊ ይህ ፈጽሞ አስጊ አልነበረም። ይልቁንም በየጊዜው እየከፋ የመጣው የአገሪቱ ፖለቲካዊ ሁኔታ በመጠኑ አስፈርቶኝ ነበር። በተለይም ገና አዲስ አበባ ሳልገባ አንድ ጋዜጣ ላይ ያነበብኩት በአዲስ አበባ 10 ሰዎች በማጅራት መቺዎች መገደላቸውን የሚገልጽ ዜና አዲስ አበባን የአደጋ እና የሞት ከተማ እንደሆነች እንዳስብ አድርጎኝ ነበር። በወቅቱ በጋዜጣ ያነበብኩት የ10 ሰዎች መገደል ታሪክ ከተማዋ ምን ያህል ሥርዓተ አልበኝነት እየተስፋፋባትና ስጋት እየጨመረ እንደሄደባት ያሳይ ነበር። በሬድዮ የሚሰማውም ሆነ በጋዜጣ የሚነበበው ሁሉ አስደሳች አልነበረም። ተማሪዎች ያምጻሉ፣ የታክሲ ሾፌሮች አድማ ይመታሉ፣ ... ብቻ ምኑ ቅጡ።

ሆኖም እግዚአብሔርም እንድሄድ ፈቃዱን መግለጽ ብቻ ሳይሆን እርሱ አብሮኝ እንደሚሄድ እያሳየ አበረታታኝ። እኔ ወደ አዲስ አበባ ስሸኝ አንድ ካናዳዊ ሚሲዮናዊ መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 91ን እና ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 43ን አንብቦ የጸለየው ጸሎት የመንፈስ ብርታትን ሰጠኝ። እኔም በዚያ ሰሞን መዝመር (121)፡1-8 ካለው ሀሳብ ላይ "እግዚአብሔር ይጠብቅሃል" የሚለውን ጥቅስ አስጽፌ ቤቱ ግድግዳ ላይ ሰቀልኩት። ከዚህም ሌላ በማቴ. 28፡20 ላይ ያለው "ሁል ጊዜ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ።" የሚል የተስፋ ቃል ፍጹም እምነት ሰጥቶኝ አጽንቶኝ ነበር። እግዚአብሔርም ፈጹም ታማኝ አምላክ ነውና በኋላ የምዘረዝራቸውን አስፈሪ ሁኔታዎች በሙሉ በድል አሻገረኝ።

ወደ አዲስ አበባ እንደገባን እኔን ደስ ለማሰኘት ብለው የጌጃ ቃለ ሕይወት መሪዎች ሊከፍሉኝ በወሰኑት በዚያ ጊዜ ጥሩ የሚባል 250 ብር ደመወዝ በ50 ብር በጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አካባቢ አነስ ያለች ጥሩ ቤት ተከራይተን መኖር በመጀመራችን ወዲያው የአገልግሎት እቅዴን አውጥቼ ወደ ሥራ ገባሁ።

በዚያን ጊዜ ጥሩ የአምልኮ ሕንፃ የተሠራላት እና ከአጥቢያይቱ አልፈው ለዋናው ቃለ ሕይወት ጽሕፈት ቤት የሚበቁ ጠንካራ መሪዎች ያሏት መሠረተ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እኔ በመጣሁበት ጊዜ 73 አባላት ብቻ የነበሯት ትንሽ አጥቢያ ነበረች። ይህንን ሁኔታ ለመቀየርም ብዙ እቅዶችን አወጣሁ። አንዱ እና ዋናውም የምሽት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መጀመር ሲሆን በወቅቱ መሪዎች ተማሪ አይገኝም ብለው ተቃውመውት የነበረ ቢሆንም በኋላ ግን ተፈቅዶ ወዲያውኑ ትምህርቱን ጀመርኩ። ግና ብዙም ሳይቆይ አዲስ አበባ እሳት ሆነች።

ያሰጋን የአዲስ አበባ ሁኔታም እኛ ከመጣንበት ጊዜ አንስቶ ከቀን ወደ ቀን እየከፋ ይሄድ ነበር። እኔም የተቀበልኳቸውን የተስፋ ቃሎች የሙጥኝ ብዬ በእምነት እና

በድፍረት አገልግሎቴን ቀጠልኩ። በእርግጥ አገልግሎት ስጀምር አብረውኝ በትጋት የሚያገለግሉ እና ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ የሚተጉ መሪዎች ነበሩ። እነ አቶ ላቀው ተሰማ፣ አቶ ብርሃኑ ደረሰ፣ አቶ ጥላሁን ኃይሌ፤ አቶ ሙላቱ ታዬ፣ ዶ/ር ሙላቱ ባፋ፤ አቶ ደምሴ ማዴ፣ አቶ ሽፈራው ወ/ሚካኤል፤ አቶ ተስፋዬ ባሀታ፣ ... በዚያ ዘመን በተለያየ የመንግስት ሥራ እና ትልልቅ ኃላፊነቶች ላይ የተሰማሩ የቤተ ክርስቲያኒቱ ታማኝ አገልጋዮች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም ከኔ ጋር የሚያገለግል ትጉሁ ወንጌላዊ ከበደ በልሁ ከጎኔ ነበር።

ከዚህ የተነሳ አገልግሎቱ ከባድ አልነበረም። እኔም አገልግሎቱን ስጀምር የምሠራውን ሥራ ዘርዝሬ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰጥቼ ስለ ነበር አስቸጋሪ የነበሩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙኝ ወዲያውኑ ቅሬታዬን እያቀረብኩ እንዲስተካከሉ ስለምናደርግ አገልግሎቱን መስመር ለማስያዝ ብዙ ጊዜ አልፈጀብኝም። በአገልግሎት የሚያግዙን በርካታ ስለነበሩ (በዚያ ዘመን ክርስቲያኖች በጣም ይተሳሰቡ ስለነበር) አዲስ አበባ ያሰብነውን ያህል አስፈሪ አልነበረችም።

እኔ እንደተለመደው በሦስት ነገሮች ላይ አተኩሬ አገልግሎት መስጠቴን ቀጠልኩ። አገልግሎት ስጀምር ጌጃ የነበሩት 73 አማኞች ብቻ ስለነበሩም በቤተ ክርስቲያኒቱ የእሁድ አምልኮ ሲደረግ የሚገኘው ሰው ብዛት በአንዱ ረድፍ እንኳን የሚሞላ አልነበረም። ይህንን ሁኔታ ያየነው እኔና ወንጌላዊ ከበደ በልሁ በአዳራሹ ውስጥ ፕሮግራም በሌለበት ቀን ማክሰኞ ማክሰኞ ባዶ ወንበሮች በሰው እንዲሞሉ እጃችንን ጭነን እንጸልይ ነበር። መንፈሳዊ ነገር የሚሠራው በሞኝነት በመሆኑ እሁድ ቀን አስተናጋጅ የሚሆን ሰው አጠጋግቶ እንዲያስቀምጥ እየነገርን ሰዉ ተጠጋግቶ ክፍት ቦታ ሳይተው ይቀመጣል። ከዚያም እኛ ባዶ የሚሆኑትን ቦታዎች መርጠን እጃችንን ለጸሎት እንጭናለን።

እግዚአብሔር የዚያን ዘመን ታሪክ ቀይሮት በጥቂት ዓመታት ውስጥ የእሁድ አምልኮአችን ሰው ጥቅጥቅ በሚልባቸው ሦስት ፈረቃዎች የሚካሄድ ሆነ።

እኔ ወደ ጌጃ እንዳመራሁ ባቀረብኳቸው ሦስት እቅዶች መሠረት አገልጋዮችን ለማዘጋጀት ዋናው መሣሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ማስተማር እንደሆነ አምን ነበር። በዚህም መሠረት ጌጃ ተተኪ አገልጋዮች እንዲኖሩ የግድ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ያስፈልጋል። ገና እንደመጣሁ ለመሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የመጀመር ሃሳብ ሳቀርብ እነርሱ ተማሪ አይኖርም የሚል ስጋታቸውን ገለጹልኝ። እኔም "የሚማሩ አምስት ሰዎች ካገኘን በቂ ነው" የሚል መልስ ሰጠሁ። በኋላም የኔም ሀሳብ የአዲስ አበባ ሰው በአብዛኛው ባለሥራ ስለነበር እቅዱ ትምህርቱ በምሽት እንዲካሄድ ነበር። መሪዎችም ብዙ ከተወያየን በኋላ ትምህርቱን መጀመሩ ጥሩ መሆኑንና ሌላው አገልግሎትም እንደማይበደል ስላመኑ እንዲጀመር ፈቀዱ። እኔ የምሽት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሳስተምር ቆይቼ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በኋላ ወደ ቤት መሄድ ጀመርኩ። በጊዜው ወታደሮች በየቦታው ይታዩ እና ሕዝቡ በስጋት ይኖር ነበር። ትንሽ ቆይቶም ሰዓት እላፊ ታውጆ ከምሽቱ ስድስት ሰዓት በኋላ መንቀሳቀስ ሁሉ ተከለከለ።

እኔ በምሽት መጽሐፍ ቅዱስ አስተምሬ ወደ ቤቴ ስመለስ ካድሬዎች እና አብዮት ጠባቂዎች በመንገዱ ላይ ይርመሰመሱ ነበር። ትንሽ ቆይቶም ሞት በየደጁ ያደባና ወጣቶች በየማታው እየተገደሉ በየጎዳናው ተጥለው ያድሩ ጀመር። እኔም ምሽት ላይ ወደ ቤቴ ስሄድ "ሞት አንድ ቀን ያገኘኝ ይሆን?" ብዬ አስብና "በቃ እኔ ብሞት የኔ መሞት ሁል ጊዜ ወንጌልን ይሠራል።" እል ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደሚጠብቀኝ የሰጠኝን የተስፋ ቃልም አልረሳሁም። እንደውም በመዝሙር (121)፡1-8 ከተጻፈው ሀሳብ ላይ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል ሰጥቶኝ "እግዚአብሔር ይጠብቅሃል!" የሚለውን ጥቅስ አስጽፌ ቤቴ ግርግዳ ላይ ሰቅዬው ስወጣ እና ስገባ አየው ነበር።

በዚህ ሁኔታ በስጋት ውስጥ እያለንም አንድ ምሽት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ዘጸአት ምዕራፍ ሦስትን አስተማርኩ። ከዚያ በዚያ ክፍል ውስጥ ያለውን ሙሴ ቁጥቋጦ ሲቃጠል ያየውን ሃሳብ በማንሳት አገልጋይ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ በእሳት ውስጥ ሊኖር እንደሚችል ነገር ግን ሙሴ ሲያየው ቁጥቋጦው በእሳት ተያይዞ የነበረ ቢሆንም እግዚአብሔር በእሳቱ ውስጥ ስለነበር ሳይቃጠል እንደሰመለሰ ሁሉ የእግዚአብሔር ሕዝብም በእሳት እና በመከራ ውስጥ እያለፈ አምላኩ አብሮት ስላለ እየለመለመ እንደሚሄድ አስተማርኩ። እኔ ይህንን ትምህርት አስተምሬ ሳልጨርስ በመኃከሉ የተኩስ ድምጽ ተሰማን። ትምህርቱን እንደጨረስንም ወደ ቤቴ በእግሬ ሄጀ ከባለቤቴ እና ከልጆቼ ጋር አምልኮ አካሂደን መዝሙር ዘምረን ተንበርክከን መጸለይ ጀመርን። ልክ በዚሁ ጊዜ ደጃፋችን ላይ ሰዎች መጥተው እንደተቀመጡ ኮቴ ተሰማን። ሰዎቹ የታጠቁ ወታደሮች ነበሩ። በጊዜው እነርሱ የፈለጉት በኛ ግቢ ውስጥ ከነበሩ ቤቶች መካከል ወጣቶች የሚያድሩበት ቤት ስለነበር እዚያ ያሉትን ወጣቶች ለመያዝ ነበር። ነገር ግን የዚያ ቤት ሰዎች በዚያ ዕለት ቀን ሰው ሞቶባቸው ወደ አገር ቤት ሄደው ነበር። በኋላም ያንን ቤት ሲያንኳኩ እኔ እየጸለይን ከነበረበት አቋርጬ ተነስቼ ስወጣ ሰዎቹም በበራፋችን ላይ በነበረ መቀመጫ ላይ ተቀምጠዋል። ገና ብቅ ስልም አንዱ ወታደር "አንተ ሰውዬ እዚህ መጨመር ካልፈለግህ ወደ ቤት ግባ" አለኝ። እኔም ወደ ቤቴ ገብቼ በር እና መስኮታችንን ዘጋጋን እና እንደገና ጸሎታችንን በኃይል ቀጠልን። በዚያ ምሽት ወታደሮቹ በዚያው ዕለት የኛ ቤት ሲቀር በግቢው የነበሩትን ሰባት ቤቶች በርብረው ከሁሉም ቤት ወጣት ወጣቱን ለቅመው ወሰዱ።

ከተወሰዱት ወጣቶች መካከል አንዳንዶቹ ኢ.ዲ.ዩ የሚባል ፓርቲ አባላት ነበሩ። ወደ እስር ቤት ተወስደው ሲቀጠቀጡ ቆይተው አንዳንዶቹ እግራቸው አንዳንዶቹ እጃቸው ተሰብሮ (ዓይናቸው የጠፋ ሁሉ ነበሩ) ተለቀቁ። አንደኛው ግን በመገደሉ ከእስር ቤት ሳይመለስ ቀረ።

በዚያን ዕለት ወታደሮቹ ወደ እኛ ቤት የመጡበት ምክንያትም እኔ በማስተማር ላይ እያለሁ ከሰማነው የተኩስ እሩምታ ጋር በተያያዘ ሲሆን በወቅቱ ተኩሱ የተካሄደው ቀበሌ ውስጥ አንድ የኢ.ህ.አ.ፓ ወይም የሰደድ ፓርቲ አባል የቀበሌውን ጸሐፊ ለመግደል ሙከራ በማድረጉ ነበር። በጊዜው ያ ወጣት ግድያውን ለመፈጸም ሽጉጥ

በቅርጫት ይዞ ሲሄድ የቀበሌው ሊቀመንበር እና አብዮት ጠባቂዎች መንገድ ተሻግረው ቆመው ነበር። እናም እርስ ወደ ቢሮ ሱተት ብሎ ሲገባ አይተውት በፍጥነት ተከትለውት በመግባት ለመሸሽ ሲሞክር ተኩሰውበት አምልጧቸው ነበር። ከዚያም እነርሱ የእርሱን ማደሪያ አጥንተው ነበር ወደ እኛ ግቢ የመጡት።

በዚህ ዓይነት በየዕለቱ በስጋት ውስጥ እያለፍኩ አገልግሎቴን ቀጠልኩ። ብዙ ጊዜ በማለዳ ከቤት ስወጣ መልካቸው የሚያማምሩ ወጣቶች ተገድለው እንደ ቆሻሻ መንገድ ላይ በቀኝም በግራም አስክሬን ተጥሎ እየተራመድኩ እሄድ ነበር።

አንድ ሌሊት በኃይለኛ ሁኔታ የተኩስ ልውውጥ እየተደረገ እኛም በተኛንበት ስንሰማ አደርን። እኔ በማግስቱ ወደ ጨንቻ (ጋሞ ጎፋ) ለአገልግሎት እሄድ ስለነበር በማለዳ ተነስቼ ወደ አውቶብስ ተራ ስሄድ መንገዱ በሬሳ ተሞልቶ ነበር። በወቅቱ የአገራችን ነበረችበት ሁኔታ በጣም ያሳዝን ነበር።

ከዚህም ሌላ እኔ በኤስ.አይ.ኤም ቢሮ ሠራተኞችን ከሥራ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምር ስለነበር ከምሽቱ 12 ሰዓት በኋላ ለአንድ ሰዓት ያህል አስተምሬ በአውቶብስ ወደ ቤቴ እመለስ ነበር። በዚህ ጊዜ እኔ ጭድ ተራ የሚባለው አስፈሪ እና ማጅራት መቺዎች የሚበዙበትን ሰፈር አቋርጬ ወደ ቤቴ ስሄድ አንድም ቀን ግልምጫ እንኳን ሳይደርስብኝ እግዚአብሔር እየጠበቀኝ እመላለስ ነበር።

# ምዕራፍ ፲፱

# በአዲስ አበባ መደላደል

## የዳዊት ሞትና የአዲስ አበባ አጽናኞቻችን

*ወ/ዊ ኬዳሞ ወደ አዲስ አበባ ካመሩ ሁለት ዓመት ሊሞላቸው በቀናት የሚቆጠሩ ጊዜያት ብቻ ቀርቷል። በዚህ አጭር በሚባል ጊዜ ውስጥም በአገሪቱ ላይ አስገራሚ እና አስደናቂ የሚባሉ ለውጦች መጥተዋል። ሥልጣን ያስረክባሉ ብለው ሲጠብቋቸው የነበሩት ንጉሥ "በሕይወት እስካለሁ ሥልጣኔን አልለቅም " ብለው ኬዳሞም "ሳይዋረዱ አይወርዱም" ብለው እንደተናገሩት በውርደት ከመንበረ ሥልጣናቸው ተነስተዋል። ኬዳሞ ለብዙ ዓመታት የንጉሉት የመሬት ለሕዝቡ የመሰጠት ጉዳይም በወታደራዊ መንግስት ምላሽ አግኝቶ "መሬት ላራሹ" ተብሎ ታውጇል። እርሳቸውና እና ቤተሰባቸው አዲስ አበባ ውስጥ ጥሩ ቤት ለማግኘት ከአንዱ ወደ ሌላው ቤት ሲንከራተቱ ቆይተው በመጨረሻ ጥሩ የምትባል ትንሽ ቤት አግኝተዋል። የከተማ ቦታ እና ትርፍ ቤቶች መወረስ አዋጅ ወጥቶም ኬዳሞ በ50 ብር የተከራዩአት ይህች ቤት የኪራይ ዋጋ ከ50 ወደ 25 በመቀነሱ አንድ ጥቅም አግኝተዋል።*

*ከበቢቾ የተንጣለለ ግቢ ኑሮ ወጥተው አዲስ አበባ በቤት የተሞሉ ግቢዎች ውስጥ ጭቃ እና ድንጋይ በለበሰ መሬት ላይ ለመጫወት የተገደዱት የቤተሰቡ ልጆችም ወደ አዲስ አበባ በመምጣታቸው የተሰማቸውን ምሬት ሲያሰሙ ሰንብተው አሁን ከተማይቱን መላመድ ጀምረዋል። በዚሁ ጊዜ የቤተሰቡ የመጨረሻ ወንድ ልጅ የሴፍ ገና ወደ አዲስ አበባ ሳይመጡ ስለ አዲስ አበባ የተነገረውን በማንሳት "አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ብላችሁ ገነት አስመስላችሁ ነግራችሁን፤ ይኸው እዚህ ብርድ፣ ዝናብ፣ ጉንፋን፣ ብቻ በሆነ ከተማ አሰቃያችሁን።" ብሎ ምሬቱን ለወላጆቹ ገልጿል። ወ/ዊ ኬዳሞ እና ወ/ሮ ታደለችም የመጡበትን የአገልገሎት ዓላማ ለልጆቻቸው በመንገር አዲስ አበባን ለማስለመድ ሲያበረታቱ ሰንብተዋል።*

*ከወ/ሮ ብዙነሽ የተገኘው የወንጌላዊ ኬዳሞ የበኩር ልጅ የሆነው ዳዊትም ኬዳሞ ባቀዱት መሠረት "እናቱ ብትሞትም አስተምሬ ለፍሬ አበቃዋለሁ" ብለው አዲስ አበባ ትምህርቱን ቀጥሎ 10ኛ ክፍል ደርሷል። በወቅቱ ዳዊት ጂ.ሲ.ኤ በሚባለው ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪ ሆኖ ነበር። ዳዊት በዚሁ ትምህርት ቤት እየተማረ እያለ አንድ ወቅት ላይ ከፍተኛ የራስ ምታት ይዞ እያሰቃየው ስለነበር ከትምህርት ቤት ቀርቶ ቤት ተኝቷል። በዚሁ ወቅት ወንጌላዊ ኬዳሞም እንዲሁ ታመው ቤት ነበሩ።*

ዳዊት በጊዜው የታመመበት ምክንያት በወቅቱ በሚማርበት ትምህርት ቤት አንድ ዕቃ ጠፍቶ የወሰደው ሰው ሳይገኝ ይቀራል። በዚሁ ጊዜ አንዲት ምዕራባዊት የትምህርት ቤቱ ባልደረባ በጥርጣሬ ስለ ዕቃው የሚያውቀው ነገር እንዳለ አጥብቃ ዳዊትን ትጠይቀዋለች።

በዚሁ ጊዜ የወንጌላዊ ልጅ እንደመሆኑ ዕቃ ቢጠፋ አንስቶ ከመስጠት ውጪ ለራሱ መውሰድን ያልለመደው ልጅ በነገሩ ክፉኛ ተጨነቀ። ይኸው ጭንቀትም ኃይለኛ የራስ ምታት አስከትሎበት ቤት እስኪያስተኛው ድረስ ጠነከረበት። ይባስ ብሎም በራስ ምታቱ ላይ ከፍተኛ ትኩሳት ተደርቦ ያሰቃየው ጀመር። ከሥራ ቀርተው ቤት በመዋላቸው ይህንን ያስተዋሉት ኬዳሞም ለዳዊትም ሆነ ለራሳቸው የሚፈውስ ወይም ሕመም ማስታገሻ መድኃኒት ለማምጣት ወደ መድኃኒት ቤት ሄደው ከቆይታ በኋላ ሲመለሱ ዳዊት ቤት ውስጥ የለም። መላ ቤተሰቡ በየአቅጣጫው ተበታትኖ ቢፈልገውም ልጁ እምጥ ይግባ ስምጥ ፈጽሞ ማወቅ አልተቻለም።

ዳዊት ያለበት ሳይታወቅ ቤተሰቡ እንደተሸበረ አንድ ቀን በጭንቅ ታድሮ በሁለተኛው ቀን እውነቱ ታወቀ። ለካስ አስቀድሞም ለቤተሰቡ ሳይናገር አማኑኤል ሆስፒታል አካባቢ ወደሚገኝ የተጠራቀመ ውሃ እየሄደ ዋና ይለማመድ ኖሯል። እናም ታምሞ እቤት በዋለበት ጊዜ ትኩሳቱ እየጨመረ ሲያሰቃየው ወደ ዋና ቦታ ሄዶ ውሃ ውስጥ ለመነከር ከቤቱ ወጥቶ ወደ እዚያ በማምራት እራሱን ለማቀዝቀዝ የገባበት ውሃ ውስጥ ሰጠመ። አብረውት ወንዙ አካባቢ የነበሩ ልጆች ለማትረፍ ቢጯጯሁም የሚረዳው እና የሚያድን ጠፍቶ ዳዊት ለዋና የገባበት ውሃ ውስጥ ሰጥሞ ሞተ። በመጨረሻም ዋናው ቦታ የነበሩት ልጆች የዳዊትን ቤት ስላላወቁ አስከሬኑን እዚያው አሳድረው በማግስቱ ሰዎች ተባብረው ቤቱን ፈልገው አገኙ።

በዚሁ ጊዜ የዳዊት አባት ኬዳም በጭንቀት ልጃቸውን ሲያፈላልጉ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ ልጁ መሞቱን ልባቸው ስለነገራቸው "ቢቃ ሞቷል" ብለውም ደመደሙ። ትንሽ ቆይቶም ልጃቸው መሞቱ እና አስከሬኑ መገኘቱ በስልክ ተገለጸላቸው።

በዚህ ጊዜ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና ያኔ የነበሯት አነስ ያለ ቁጥር ያላቸው አባላት በሙሉ እንደ አንድ ሰው ሆነው ከወንጌላዊው ቤተሰብ ጋር ቆሙ። በተለይም ከዘመድ ከወዳጅ ተለይቶ መጥቶ ገና በአዲስ አበባ ከተማ ኑሮን በመለማመድ ላይ የነበረውን ቤተሰብ ብቸኝነት እንዳይሰማው ለማድረግና በደረሰውም አስደንጋጭ አደጋ በጣም አዝነው ለማጽናናት ተሰባሰቡ። አስከሬኑም በጌጃ አባላት ታጅቦ ወደ ቤት መጥቶ ለቀብር ዝግጅት ተጀመረ። አብዛኛው አባላትም አስደንጋጩን ሁኔታ በማሰብ የኬዳሞን ቤተሰብ ለማጽናናት እና የቀብር ሥነ-ሥርዓቱን በተሳካ ሁኔታ ለማስፈጸም መሰናዶአቸውን ቀጠሉ።

በዚሁ ጊዜ የልጃቸው ሞት ኃዘን ላይ የነበሩት ኬዳሞ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ በመንፈስ ቅዱስ አሳሳቢነት ወደ ልቦናቸው መጣ፦

> "እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤ በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል፤ በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን። ይህም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን መከራ ትዕግስትን እንዲያደርግ ትዕግስትም ፈተናን፣ ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን በመከራችን ደግሞ እንመካለን፤ በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም "
> ሮሜ. 5፡1-5

*ከዚህ በኋላ ከጥልቅ የኃዘን ስሜት ወጥተው አጽናኞቻቸውን ሊያጽናኑ ተዘጋጁ። ወዲያውም ተነስተው ይህንኑ ቃል በመስበክ ሕዝቡን ካጽናኑ በኋላ ለቅሶ ደራሹ ሕዝብ ተረጋግቶ ተቀመጠ።*

*በአዲሱ የቤተ ክርስቲያናቸው አገልጋይ ላይ የደረሰው አሳዛኝ ገጠመኝ ልባቸውን የነካው የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ወንጌላዊውን ቀርበው አነጋገሩ። "አስከሬኑ የት እንዲቀበር ትሻለህ? አገር ቤት ወስደ እቀብራለሁ ካልክም እኛ ካንተ ጋር አብረን ወስደን እናስቀብራለን። እዚሁ ይሁን ካልክም ሃሳብህን አሳውቀን።" አሉአቸው። ወንጌላዊውም በዚህ ጊዜ ተነስተው ንግግር አደረጉ። አስቀድመውም በጸሎት እግዚአብሔርን ስለሁሉ አመሰገኑ። ከዚያም "እኔ ልጄ ዳዊትን እናቱ በሞት ስትለየኝ ከኔ ልለየው አልፈለግኩም። ከ5 ዓመቱ ጀምሮም እናቱ በሌለችበት ከኔ ጋር አብሮኝ ዞሯል። እኔም እርሱን እንደሚገባ አሳድጌ አንድ የክብር ስፍራ አደርሰዋለሁ የሚል እምነት ነበረኝ። ነገር ግን የዳዊት መጨረሻ እንደዚህ ሆነ። ስለዚህ ከዚህ በኋላ የልጄን አስከሬን ወደ የትም አልወስድም፤ እዚሁ እቀብራለሁ" አሉ።*

*ወዲያውም ዘመድ ሰምቶ እንዲመጣ በዚያ ዘመን በነበረው ልማድ መሠረት "የኬዳሞ ልጅ ዳዊት ስለሞተ ነገ የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ይፈጸማል።" ተብሎ በሬዲዮ እንዲነገር ተደረገ። የወንጌላዊ ኬዳሞ የቅርብ ዘመዶችም በዚያው ዕለት ማታ ተነስተው ሆሳዕና ከተማ ገብተው በማደር በማግስቱ ለቀብሩ አዲስ አበባ ተገኙ። የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና አባላትም ኃዘኑን የራሳቸው አድርገው ሁሉን በማስፈጸማቸው የቀብሩ ሥነ-ሥርዓት በመልካም ሁኔታ ተካሄደ።*

*ኬዳሞም በጊዜው የነበሩ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ሃይሎች ወጣቶችን በኃይል ይፈልጉ ስለነበር ልጃቸው አንዳች አደጋ እንዳይገጥመው እቤት ውስጥ ሲጫወት እንዲውል ልዩ ልዩ መጫወቻዎችን ለማዘጋጀት እየጣሩ ከአደጋ ለመጠበቅና እንደሚገባ እግዚአብሔርን አውቆ እንዲያድግ ጥረት ሲያደረጉ ቆይተዋል። ሆኖም ዳዊት በድንገት በአደጋ ሲለያቸው በልባቸው አንድ ነገር አሰቡ። "ልጄ ምናልባት አድጎም እኔ እንደተመኘሁት ለእግዚአብሔር ክብር የማይሰጥ ሊሆን ይችላል። ምናልባት ለዚህ ይሆናል እግዚአብሔር በጊዜ ሊወስደው የወሰነው " ሲሉ ከራሳቸው ጋር አወሩና ፍጹም ተጽናኑ። በጌጃ አጥቢያና በአካባቢው የጀመሩትን የወንጌል አገልግሎትም በቀደመው ትጋታቸው ቀጠሉ።*

## የአዲስ አበባው ኑሮ ሲጀመር እንዲህ ነበር

የልጄ የዳዊት ሕልፈተ ሕይወት አዲስ አበባ ከገባን ሁለተኛ ዓመታችንን ልንደፍን ቀናት ብቻ ሲቀሩ ያጋጠመን ሲሆን ይህ ሁኔታ እግዚአብሔር በጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሰጠንን ወንድሞች እና እህቶች ፍቅርን ያየንበት አጋጣሚ ነበር። ለነገሩ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አባላት እና መሪዎችን ጥልቅ ፍቅር ለመጀመሪያ ጊዜ ያየነው በዚህ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ገና በ1965 ዓ.ም ጳጉሜ ወር ወደ አዲስ አበባ ስንመጣ የጀመረ ነበር።

በቀደሙት ዓመታት በቦቢቾ የራሳችንን ቋንቋ በሚናገር ሕዝብ መካከል አስደናቂ የአገልግሎት ዘመን አሳልፈአለሁ። በቢቾ ባሉኝ አገልግሎቶች መልካም ፍሬ እየታየ፤ ብሎም ሆሳዕና ከተማ ወንጌል እንዲሰፋ እና ያመኑት እንዲበረቱ እግዚአብሔር

ምክንያት እያደረገኝ፤ ከዚያም ባሻገር በመላው የአገራችን ደቡባዊ ክፍል እና በአዲስ አበባ ሳይቀር እየተዟዟርኩ ፍሬያማ የወንጌል አገልግሎት ዘመናትን አሳልፌያለሁ። አሁን ደግሞ ወደ አገሪቱ መናገሻ ከተማ በአዳዲስ ሕዝብ መካከል ሙሉ በሙሉ የከተማ በሆነ ባህል ውስጥ ለማገልገል ተነሳሁ።

ቤተሰባችን ወደ አዲስ አበባ ሲዛወር ዝግጅታችን ከተጠናቀቀ በኋላም እኔ አስቀድሜ በያዝኩት እቅድ መሠረት ለአንድ ወር የአሩሲ ክፍለ አገር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥልጠና ነሐሴ ወር ላይ ወደ ኩየራ ሄድኩ። በወቅቱ የኔ ትልቅ የጸሎት ርእስ የነበረውም አዲስ አበባ የሚኖረን ቆይታ በዚያ አገሪቱ ባልተረጋጋችበት ወቅት እኛ ከገጠር የመጣን ሰዎች እንዴት እንሆናለን የሚል ነበር። አስቀድሜ እንደጠቀስኩት በኩየራ የአገልግሎት ቆይታዬ ማብቂያ ላይ አንድ ፈረንጅ ያስተማረው እና ያነበባቸው ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ትልቅ የመበረታታ መልእክት ሆነውልኛል።

በመጨረሻም ባለቤቴ ከሰባቱ ልጆቻችን ጋር ጳጉሜ 2 በአውቶብስ ከሆሳዕና ተነስተው እንዲመጡ በተነጋገርነው መሠረት ወደ አዲስ አበባ መጡ። እኔም አስቀድሜ ከኩየራ ወደ አዲስ አበባ ከመምጣቴ በፊት ለአንድ ወር ቆይታ ወደ ኩየራ በአዲስ አበባ በኩል አድርጌ ስለሄድኩ አስቀድሜ አየለ ቀልበሮ፣ እቴቱ እና ሌሎችም ጉጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ያገኘኋቸውና በፊትም የማውቃቸውን ወገኖችን ቤት ተከራይተው እንዲጠብቁኝ ነግሬ ነበር። እነርሱም እንደነገርኳቸው ቤት ተከራይተው ነበር የቆዩኝ።

በዚህ ጊዜ ወ/ሮ ብዙነሽ የምትባል ከብዙ ዓመታት በፊት የማውቃት እህት እና ባለቤቷ ታምራት እሳቱ በራሳቸው መኖሪያ ቤት የእንግዳ ማረፊያ ስለነበራቸው ቤት ተከራይተን የራሳችንን ኑሮ እስክንጀምር ድረስ እዚያ ገብተን እንድናርፍ አስበው ነግረውኝ ነበር። እኔ ግን ወደ እዚያ ቤት መግባት ከብዶ ስለታየኝ ወዲያውኑ አይሆንም ብዬ ማሳመን የምችልበት ለእነርሱ አጥጋቢ የሚሆን ምክንያት ስለሌለኝ እሺም እምቢም ሳልል ቆየሁ።

በጊዜው እኔ እነርሱ ወዳዘጋጁልኝ እንግዳ ማረፊያ ለመግባት ከብዶ የታየኝ የኛ ብዙ ቁጥር ያለው ቤተሰብ፣ ከገጠር የመጣ የአዲስ አበባን የከተሜ አኗኗር ያልለመዱ ልጆቼ ከነ ጉንፋናቸው እና ሌላም ሌላም የገጠር ልምዳቸው ወደ እነርሱ ዘመናዊ፣ ጽዱ እና የተዋበ የከተማ ቤት ሲገቡ ሁኔታው ምቹ እንደማይሆን ስለገባኝ ነበር። እናም እነ አቶ አየለ ቤት አይተው የኪራይ ውል ፈጽመው እንዲጠብቁኝ አድርጌ እኔ አስቀድሜ አዲስ አበባ መጥቼ ሁኔታውን አመቻቸሁ። በእርግጥ የተገኘው ቤት ጽዱ እና ጥሩ የሚባል ዓይነት አልነበረም። በተለይ ግቢው እና ደጃፉ ቆሻሻ እና ሽታ ያለው ነበረ። ነገር ግን ለአንድ ወር አማራጭ ስለሌለን ተረጋግተን ሌላ ቤት እስክንፈልግ ይሁን ብዬ ባለቤቴ እና ልጆቼን ለመቀበል አዘጋጀሁት።

ባለቤቴ እና ልጆቼ አዲስ አበባ አውቶብስ ተራ በሚደርሱበት ሰዓትም እነርሱን ለመጠበቅ በዚያ ዘመን የነበረ ሴቼንቶ የሚሉትን የኮንትራት ታክሲ ተኮናትሬ ሄድኩ። አቶ ታምራት እና ባለቤቱም ቀኑን ሙሉ ሲደውሉ ዝም ብዬ መልስ ሳልሰጥ ቆየሁ።

አቶ ታምራትም ቤተሰቤን በሙሉ ሊጭን የሚችል ተለቅ ያለ አዲስ መኪና ከሹፌር ጋር አዘጋጅቶ ለመቀበል ሲጠብቁ ነበር። በኋላም ሁሉ ከተጠናቀቀ በኋላ ስልክ ሲደውሉ አንስቼ እነ አየለ ቤት ተከራይተውልን እዚያ ገብተናል ብዬ ነገርኳቸው። አቶ ታምራት እና ባለቤቱም በኮንትራት ታክሲ ቤተሰቤን ጭኜ ወደ ተከራየሁት ቤት መሄዳችንን ሲሰሙ እርሱ እና ባለቤቱ ወደ ቤታቸው ሄደው እኛን ተቀብለው ለማስተናገድ ያዘጋጁትን አይነተ ብዙ ምግብ ጭነው ወደ አዲሱ ቤታችን መጡ። በዚሁ ጊዜ የጎጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ባለቤቶቻቸው የሆኑት እነ ወ/ሮ ወተቱ፣ ወ/ሮ ፊትለ፣ ወ/ሮ መንበረ፣ ወ/ሮ ቀለሟ እና ሌሎችም አዲስ ቤት ለሚገባ ሰው ያስፈልጋል ብለው ያሰቡትን ብዙ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁስ ገዝተው ስጦታ አበረከቱልን።

ከዚያም እነዚህ እህቶች ባመጧቸው የወጥ ቤት እና የመመገቢያ ዕቃዎች ተጠቅመው እነ አቶ ታምራት ያመጡትን የተትረፈረፈ ምግብ አቅርበው በቤታችን ከታላቅ ግብዣ የማይተናነስ መስተንግዶ ተደረገ። ለእኛም ትዝታ የሚጥል አስደሳች አቀባበል ሆነልን። የጎጃ እህቶች ያመጡአቸው የቤት ዕቃዎችም አንዳንዶቹ ዛሬም ድረስ በቤታችን ውስጥ ያሉ ለረጅም ዘመናት የተገለገልንባቸው ጠቃሚ ስጦታዎች ሆነውናል።

እነ አቶ አየለ የተከራዩልን ቤት የአካባቢውም ሆነ የቤቱ ጽዳት ብሎም የመጸዳጃ ቤቱ ሁኔታ ጥሩ ስላልነበር ለአንድ ወር ብቻ ቆይተንበት ወደ ሌላ የተሻለ ቤት ተዛወርን። በጊዜው ለሁለተኛ ጊዜ የተከራየነውን ቤትም ብዙም ሳንቆይበት ወደ መካኒሳ አካባቢ ሌላ ቤት ተከራይተን ገባን። ሆኖም እንደገና በዚያው ቤት በቀየርንበት 1967 ዓ.ም እኔ የጎጃ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የማስተማር ሥራን በማታው ክፍለ ጊዜ በመጀመሬ አምሽቶ ለመግባት ስላላመቸኝ በ1970 የራሳችንን ቤት ገዝተን ቫቲካን ኢምባሲ ጀርባ ወደ አለው ቤታችን እስክንዛወር ድረስ ወደ ጎጃ ሰፈር ተመልሰን ለሦስት ዓመታት ያህል ኖርን። አስከፊው ቀይ እና ነጭ ሽብር ኢትዮጵያውያን የተላለቁበትን የስጋት ዘመንም እዚያው ከተማው መኃል እየኖርን የዓይን ምስክሮች ሆነን።

## አዲስ አበባና ቤተሰባችን

አዲስ አበባ እንድመጣ እና እንዳገለግል የቀረበልኝን ጥያቄ ለመቀበል ከወሰንኩ ጀምሮ ለልጆቻችን አዲስ አበባ ልንሄድ እንደሆነ፤ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ እንደሆነች፣ ሕዝቡ የሰለጠነ፣ ትምህርት ቤቶቹ ቆንጆ፣ ቤተ ክርስቲያናቱና መኖሪያ ቤቶቹ ሁሉ የሚያምሩ ሰማይ ጠቀስ ህንጻዎች የሞሉባትና መኪኖች የሚበዙባት ዘመናዊ ከተማ እንደሆነች እኔም ባለቤቴም ነግረናቸው ነበር። ይሁንና ወደ አዲስ አበባ የመጣነው የዓመቱ መጀመሪያ አካባቢ ቢሆንም ልጆቻችን የከተማይቱን ብርድ እስኪለምዱ ድረስ ቶሎ ሊወዷት አልቻሉም ነበር። በተለይም አስቀድመን የገባንበት ቤት እና በመጀመሪያ አካባቢ የኖርንበት የጎጃ ሰፈር በአንድ ግቢ ብዙ ሰዎች

የሚኖሩበት አኗኗር ለእነርሱ ከበቢቾ የተንጣለለ ግቢ ኑሮ ጋር ስላልተመሳሰለ ለመልመድ ችግሯቸው ሲጨነቁ ዓላማችን የምቾት ኑሮ ፍለጋ ሳይሆን ለአገልግሎት እንደሆነ በመንገር እያስረዳናቸው ቆየን።

በዚሁ የአዲስ አበባ ኑሮ ጅማሬ ላይ ከልጆቼ እና ከባለቤቴ ጋር ተስማምተን አንድ ውሳኔ ላይ ደረስን። አዲስ አበባ ውስጥ ሰው ሁሉ አማርኛ ስለሚናገር ልጆቻችንም አማርኛ ቶሎ ለመዱ። ነገር ግን ሁል ጊዜ አማርኛ ብቻ የሚናገሩ ከሆነ ወደ አገር ቤት ሲሄዱ እና ከገጠርም ዘመዶቻቸው ሲመጡ ሃዲይኛ ብቻ ከሚናገሩት ጋር መግባባት ያቅታቸዋል። ስለሆነም እኔ "እናንተ ወደ ገጠር ስትሄዱም ሆነ፤ ዘመዶቻችሁ ከገጠር ሲመጡ እንዳትቸገሩ አማርኛ ሌላ ቦታ እንደልብ ተናገሩ፤ እቤት ውስጥ ግን ሁል ጊዜ ሃዲይኛ ብቻ እንነጋገር" ብዬ አሳምኜአቸው ነበር። ከዚያ ጊዜ ጀምሮም ልጆቼ ሙሉ ሰው ሆነው ቤት ሲመጡ ሁሉ ቤታችን ውስጥ በሃዲይኛ ብቻ እንነጋገር ነበር። ከዚህም የተነሳ ወደ አዲስ አበባ ስንመጣ የ3 ዓመት ሕፃን የነበረችው ልጄ ምህረት ሳትቀር ሃዲይኛ አቀላፋጥ ትናገራለች።

ከዚሁ ጋር በተያያዘም ሐኪም የሆነው ልጄ ተክለ አብ ሆሳዕና ሆስፒታል በሚሠራበት ወቅት የገጠመውን ነግሮኛል። አንድ ወቅት ታካሚዎችን እየተቀበለ በማስተናገድ ላይ ሳለ አንድ አባት መጥተው በተሰባበረ አማርኛ ችግራቸውን ሊያስረዱት ሲታገሉ "አባባ አይቸገሩ በሃዲይኛ ይንገሩኝ" ይላቸዋል። እኚህ አባትም በጣም ተደስተው "አንተም የኛ ሰው ነህ?" ብለው በመደነቅ በሃዲይኛ አናግረውት በቀላሉ ተግባብተው ሊረዳቸው ችሏል።

# ምዕራፍ ፳

# ጌጃ የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋም GBI

*ጊዜው የ2006 ዓ.ም ማብቂያ የዝናባማው ሐምሌ ወር አንድ ዕለት ነው። ቀደምቷ የአዲስ አበባ ከተማ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ጌጃ ቃለ ሕይወት የበዓል ሽርጉድ ላይ ነበረች። ቅጥር ግቢው ደጃፍ ላይ የተሰቀለ ትልቅ ፖስተርም የቤተ ክርስቲያኒቱ መጽሐፍ ቅዱስ ተቋም ለመጀመሪያ ጊዜ በአማርኛ ቋንቋ በዲግሪ መርሃ ግብር ያስተማራቸውን ተማሪዎች ከሌሎች የዲፕሎማ ተማሪዎች ጋር የሚያስመርቅበት የአዲስ ምዕራፍ ጅማሬ ቀን መሆኑን ያበስራል። በእርግጥ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ከቅርብ ዓመታት በፊት በርካታ አጥቢያዎችን በመላው አዲስ አበባ እየወለደች ተክላ የድሮ አቅሟ የቀነሰ የሚመስልበት እና የኮምኒስቱ መንግስት ዘመን የተጋጋለ እንቅስቃሴ ጋብ ብሎ የቆየባቸው የሚመስሉ ዓመታትን አልፋ እንደ አዲስ መነቃቃት የጀመረችበት ጊዜ የመጣ ይመስላል።*

*ስለዚህ ሳይሆን አይቀርም ቤተ ክርስቲያኒቱ ቀደም ብሳ ደመቅ ያለ ክብረ በዓል በማዘጋጀት ባሳለፈችው የ58 ዓመታት የአገልግሎት ቆይታ ውስጥ የሳቀ ዋጋ የከፈሉ መሪዎችን እና እንደ እነ ወንጌላዊ ኬዳሞ ያሉ አገልጋዮች ያበረከቱትን አገልግሎት እና የከፈሉትን ዋጋ ዘክራለች። የቤተ ክርስቲያኒቱ አንጋፋ የመዘምራን ቡድንም 40ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን ለማክበር ደፋ ቀና ማለት ጀምሯል።*

*በዚሁ መኃልም ቀደም ብሎ ቤተ ክርስቲያኒቱ እንደገና ትልቅ ትኩረት የሰጠችው እና የራሱ መገልገያ ግቢ እንዲኖረው ከቤተ ክርስቲያኒቱ ቅጥር ግቢ ውጪ ያለ ቦታ የተገዛለት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተቋም GBI (Geja Bible Institute) በሚል ስያሜ በአዲስ መልክ ተደራጅቶና ተጠናክሮ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል።*

*በዕለቱ ተቋሙ የመጀመሪያ የዲግሪ ተማሪዎቹን ሊያስመርቅ ብሎም 40ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን ሊያከብር ቀን ተቀጥሮ እንደገና በትንሿ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ሕዝብ ተሰበሰበ። በዕለቱ ከተማሪዎች ምረቃ ሥነ ሥርዓት አስቀድሞ ተቋሙ እያደረገ ስላለው የዕድገት ጉዞ በተቋሙ የቦርድ አመራሮች ገለጻ ተሰጠ። ተቋሙ ለቤተ ክርስቲያን እና ለወንጌል መስፋፋት ያበረከተው ከፍተኛ አወንታዊ ተጽእኖ በትውስታ ተወሳ።*

*በአርግጥም የጌጃ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከመላው የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት እና አንዳንዱም ከክፍለ ሀገር ከተሞች ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ አገልጋዮችን መጽሐፍ ቅዱስ በማስተማር ትልቅ አገልግሎት ሰጥቷል። በስደቱ ዘመን ቤተ ክርስቲያናት ተዘግተው መጽሐፍ ቅዱስ ለመማር አማራጭ ባልነበረበት ጊዜም ሆነ በአሁኑ ዘመን የዕምነት ነጻነት ታውጆ ሰዎች ያለ ክፍያም ሆነ በክፍያ መንፈሳዊም ሆነ ዓለማዊ ትምሕርት ለመማር አማራጭ በበዛበት ሁኔታ ውስጥ ተቋሙ በርካታ መጽሐፍ ቅዱስን የመማር ጥማት ያላቸው ተማሪዎችን እየተቀበለ በማስተማር ለተሻለ አገልግሎት አብቅቷል።*

*በአሁኑ ወቅት በመላው አዲስ አበባ እና በበርካታ ሌሎች ከተሞች የሚገኙ የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋዮች እና ቁጥራቸው የበዛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ ተቋም መጽሐፍ ቅዱስን የመማር ዕድል ,የገኙ ናቸው። በተለይ ከጌጃ በወጡ አዳዲስ የአዲስ አበባ ቃለ ሕይወት አጥቢያዎች በመሪነትም ሆነ በሙሉ ጊዜ አገልጋይነት የሚያገለግሉ በርካታ አገልጋዮችን በቀላሉ መቁጠር ይቻላል። ከዚህ በማይተናነስ ሁኔታም በልዩ ልዩ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉ በርካታ አገልጋዮች በዚሁ ተቋም የመማር እና ለአገልግሎት የመዘጋጀት እድል አግኝተዋል።*

*የጌጃ የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋም መሪዎች ተቋሙ እያደረገ ስላለው የዕድገት እንቅስቃሴ እና በዓመታት መካከል ስለነበረው አገልጋዮችን በቃሉ እውቀት የማስታጠቅ ሚና ካወሱ በኋላ በዕለቱ የሚከናወን አንድ ፕሮግራም እንዳለም ገለጹ። በጊዜው ይህ ሁሉ እንዲሠራ የዕለቱ ክብረ በዓል እንዲከበርም መነሻ የሆኑት ዛሬ ይህ ሊሆን እንደሚችል አስበው ሳይሆን በነበሩበት ዘመን ቤተ ክርስቲያን የነበራትን ክፍተት በማየት ተተኪ አገልጋዮችን ለማፍራት በማሰብ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱን የከፈቱ እና የመጀመሪያው መምህር እና ርዕሰ መምህር በመሆን ላደራጁት ሰው ተቋሙ እውቅና ሊሰጥ እንደሚወድ ተገለጸ። እናም ተቋሙ በመጀመሪያ የድግሪ መርኃ ግብር ተማሪዎችን ሲያስመርቅ ለአንጋፋው የተቋሙ መስራች እና ለ16 ዓመታት ያህል ሲያስተምሩ እና ሥራውን ሲመሩ ሽቆዩ ባለውለታውም የክብር ዲግሪ በመስጠት እውቅና እንደሚሰጥ ተበሰረ። በዚህም መሠረት ወንጌላዊ ኪዳሞ ሞቅ ባለ አቀባበል ከመንበራቸው ተነስተው የክብር ዲግሪአቸውን ከዕለቱ የክብር እንግዳ እጅ ተቀበሉ። በዚህ ክብረ በዓል ላይ እርሳቸው እና ሌሎች ተባባሪ አገልጋዮች ለተቋሙ እድገት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ የሚያስቃኝ የግማሽ ሰዓት ዘጋቢ ፊልምም ለእይታ በቅቷል።*

## የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ቤት መክፈት

እኔ በልዩ ልዩ የአገሪቱ ክፍሎች ዞሬ አገለግል በነበረበት ዘመን አበይት ዓላማዎቼ አድርጌ በማነሳቸው ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ላይ ትኩረት አድርጌ መስራትን እሻለሁ። ይህንን ተግባራዊ ሳደርግም በትክክል እግዚአብሔር እኔን በላከኝ ስፍራ እንዲሆን የሚፈልገውን ፍሬ አያለሁ። ጌጃ ሳለሁ እንዲሁ ሦስቱን ነገር ማሳካትን ዋና ዓላማ አድርጌ ተነሳሁ። ከወንጌል ሥርጭትም አንጻር በኋላ የምተርክላችሁን ስልት የቀየስን

ሲሆን ያመኑትን ለማስተማርም እንዲሁ በርካታ ዘዴዎችን ቀይሰናል። ተተኪ አገልጋዮችን ማዘጋጀት ግን ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊሠራ የሚገባው አንድ ነገር ሆኖ ታየኝ።

የወንጌል አገልጋይ ሆኜ ጥሪዬን አውቄ እንድሰማራ ከዚያም አገልግሎቱን እንደሚገባ እንድሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መማሬ ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳደረገልኝ አውቃለሁ። በቢቾ ገቢም ሆነ ዱራሜ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከተማርኩ በኋላ እኔ ያገኘሁትን እውቀት ለሌሎች ለማካፈል መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማር ሥራዬ አድርጌ ቆይቻለሁ። ቡተለይ ከዱራሜ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ስመረቅ አቅጄ የነበረው በሻሾጎ ምድር የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ማቋቋም ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነ እና ከተቋቋመ ወደ ቆየው እኔም ወደ ተማርኩበት በቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሄጄ እንዳስተምር እና በምክትል አስተዳዳሪነት እንድሠራ ሆነ።

ወደ ጌጃ ተዛውሬ አገልግሎት ከጀመርኩ በኋላም ነገ ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚረከቡ አገልጋዮችን ከማዘጋጀት አንጻር አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ ብዬ ያሰብኩትም ይህንኑ ራእዬን ለማሳካት ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መክፈትም አማራጭ የማይገኝለት ዋነኛ ተተኪ አገልጋዮችን የማዘጋጃ መንገድ ሆኖ ታየኝ። ይህንኑ ጉዳይም ሳልውል ሳላድር ተግባራዊ ሳደርገው ተነሳሁ።

የጌጃ አገልግሎቴን በ1966 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ጀምሬ ገና አራት ወር እንኳን ሳይሞላኝ የማታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለመጀመር ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥያቄ አቀረብሁ። በዚህ ጊዜ እኔ ጥያቄዬን ሳቀርብ የራሴንም ሁኔታ ተመልክቼ ነበር። ወንጌላዊ ከሌላ ቦታ ሲመጣ ገና ቤተ ክርስቲያኒቱን እና አባላቷን እስኪያውቅ፤ የተለያዩ የከተማዋን የአኗኗር ሁኔታዎች ማወቅ፤ መለማመድ እንዳለበትና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በተሟላ ሁኔታ ማገልገል እንደሚጀምር ተረድቻለሁ።

ስለዚህ በጥያቄዬ ላይ "ከዚህ በኋላ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከገጠር አይመጣም። እዚሁ አስተምረን እናዘጋጃለን።" ብዬ ነበር።

ይህንን የሰሙት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም እኔ ከገጠር በመምጣቴ ስለተቸገርኩ እና በእነርሱ የተበደልኩ አድርጌ እንደተናገርኩ አስበው በጥያቄዬ ተደናገጡ። እኔም ጥያቄዬ ከአገልግሎቱ አስፈላጊነት አንጻር እንጂ ከኔ ጋር የተያያዘ እንዳልሆነ አስረዳሁ። ነገር ግን ከሁኔታው የተነሳ እኔና ቤተሰቤ እንዴት የአገር መለዋወጡን ለመልመድ እየተቸገርን እንዳለ፤ አዲስ አበባ ቤት ማግኘት ቀላል እንዳልሆነ ሌላም ሌላም ሀሳብ እያቀረብኩ ችግሩን ነገርኳቸው። በጊዜው ለመሪዎቹ መጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ቤት የመክፈቱ ሃሳብ እንግዳ ነገር ሆነባቸው። የአዲስ አበባ አገልጋይ ቢገኝ በራሱ ቤት ወይም በቤተሰቡ ቤት ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል እና ብዙም ችግር እንደማይኖርበት፤ በዚህቹ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ እዚሁ ሁሉን ነገር እያወቀ እየለመደ

ከሰውም ጋር ተዋውቆ እንዲያድግ ለማድረግ እንደሚቻል እና አገልግሎት ለመጀመር እንደማይቸገር ነገርኳቸው።

መሪዎቹ ግን የኔ ሃሳብ 70 ያህል አባላት ብቻ በነበራት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሳካቱ አጠራጠራቸው። እናም በወቅቱ ከመሪዎቹ አንዱ የነበሩት አቶ ብርሃኑ ጥያቄዬን በጽሑፍ እንዳቀርብ እና በጽሑፌ ውስጥም መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መክፈት የሚያስፈልግባቸውን ምክንያቶች ዘርዝሬ እንዳብራራ ጠየቁኝ። እኔም እንደተጠየቀው መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በጌኛ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መክፈት ያስፈለገባቸውን 3 ምክንያቶችን ጠቅሼ በጽሑፍ አቀረብኩ። ሦስቱም ምክንያቶች እነዚህ ነበሩ፡-

1ኛ. ሰዎችን በእግዚአብሔር ቃል እውቀት ማሳደግ እንችላለን።

2ኛ. የሰዎችን መንፈሳዊ ሕይወት ለማሳደግ እንችላለን።

3ኛ. ተተኪ አገልጋዮችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልናፈራ እንችላለን።

በዚህ ጊዜ መሪዎች ይህንን ሃሳብ ተግባራዊ እንዳይሆን ሊያደርጉ የሚችሉ ነገሮችን እያነሱ ጥያቄ አቀረቡልኝ። የመጀመሪያው "የአዲስ አበባ ሰው በሥራ፣ በግል ጉዳይ፣ በትምህርት የተያዘ እና ከሩቅ አካባቢ ሳይቀር የሚመጣ ስለሆነ በምሽት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የሚማር ሰው ለማግኘት ስለሚያስቸግር ሰው አይገኝም" አሉ። እኔም "ትምህርቱን ለመጀመር 3 ሰው ካገኘን ይበቃል" አልኩ። ለሁለተኛ ጊዜ መሪዎች አስተያየታቸውን ተከትሎ "ለትምህርት ቤቱ የሚያስፈልጉ መጻሕፍት፣ በቂ መምህራን እና የመማሪያ ክፍሎች እንዴት እናገኛለን?"፣ ሲሉ ጥያቄ አቀረቡ። እኔም "የማስተማሪያ መጽሐፍትን በተመለከተ እኔ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ስማር የተማርኩባቸው እና እስከ አሁን ያቆየኋቸው ስላሉኝ እነሱን እንጠቀማለን። በተጨማሪም ከበደ በልሁም ጅማ መጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ቤት የተማረባቸው መጻሕፍት አሉት። ደግሞም እርሱ እና እኔ መምህራን እንሆናለን። ኤስ. አይ. ኤም. ያሉ ሰዎችም እንዲያስተምሩ እና መጻሕፍት እንዲለግሱ እንጠይቃቸዋለን። ትምህርቱን ስንጀምርም በመጀመሪያ የሚያስፈልገን አንድ ክፍል ብቻ ይሆናል። አንድ ጊዜ ተማሪዎችን ተቀብለን ሌላ ሳንጨምር ለሦስት ዓመት እነርሱን ብቻ እናስተምራለን።" ብዬ ስላረዳኋቸው በመጨረሻ ፈቀዱ።

ወዲያው ሀሳቡ ጸድቆ በቤተ ክርስቲያን አምልኮ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሊጀመር እንደሆነ እና መማር የሚፈልጉ እንዲመዘገቡ ማስታወቂያ ሲነገር ለመጀመሪያ ጊዜ ለመማር 63 ተማሪዎች ተመዘገቡ። እኛም ለትምህርቱ ሥርዓተ ትምህርት (ካሪኩለም) አዘጋጅተን በየምሽቱ ከ12 ሰዓት እስከ 2 ሰዓት ድረስ ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ ማስተማር ቀጠልን።

በጊዜው ለትምህርቱ ከተመዘገቡት መካከል እነ ወ/ሮ ቀለሟ ኃይሌን የመሳሰሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆኑ አባላት ነበሩ። እግዚአብሔር ረድቶንም ምንም እንኳን

ጊዜው መሸቶ ወደ ቤት ለመሄድ ምቹ ባይሆንና የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ብዙ ዓይነት ኃላፊነቶች ቢኖሩባቸውም ብዙዎች ቃሉን ለመማር ጥማት ስለነበራቸው ትምህርቱን ከጀመሩ 63 ተማሪዎች 27ቱ በሚገባ ተምረው በማጠናቀቅ ተመረቁ፡፡

እኛም የትምህርቱን ደረጃ እና ጥራት አሻሽለን ለመቀጠል የመጡትን አመልካቾች ሁሉ ከመቀበል ይልቅ ባለ ሰባት ነጥብ መስፈርት የተማሪዎች ቅበላ መመዘኛ አዘጋጀን፡፡ በጊዜው ያወጣናቸው ሰባቱ የመመዘኛ ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ፡-

1ኛ. ጌታን ካመነ በኋላ ለ5 (አምስት) ዓመታት ያህል የቤተ ክርስቲያን አባል ሆኖ/ና የኖረ/ች፣

2ኛ. ጌታን ካመነ/ች በኋላ በሕይወቱ/ቷ ምን አይነት መከራዎችን ስለ ክርስቶስ እንደተቀበለ/ች እና እንዴት እንዳለፋቸው/ፈቻቸው መግለጽ የሚችል/የምትችል፣

3ኛ. ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር መልካም ግንኙነት ያለው/ያላት እና በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተበድያለሁ ብሎ/ላ የማይ(ት)ናገር/ መሪዎችን የማይ(ት)ወቅስ፣

4ኛ. ቢያንስ እስከ 6ኛ ክፍል ድረስ የተማረ/ች፣

5ኛ. በአዲስ አበባ እራሱ(ሷ)ን እያስተዳደረ/ች የሚ(ምት)ገኝበትን የሥራ ሁኔታ መግለጽ የሚ(ምት)ችል እና የሥራው/ዋ ሁኔታ ለትምሕርቱ/ቷ እንቅፋት የማይሆንበ(ባ)ት፣

6ኛ. ለትምህርቱ የሚያስፈልገው/ጋት በቂ ጊዜ ያለው/ላት፣

7ኛ. ከቤተ ክርስቲያን የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚ(ምት)ችል፣ የሚሉ ነበሩ፡፡

ትምህርቱንም እያሻሻልን ሄደን ወደ አራት ዓመት የማታ የዲፕሎማ መርኃ ግብር ትምህርት በማሳደግ ሥርዓተ ትምህርቱን በደንብ አዘጋጀን፡፡ በጊዜው ከእኛ ባሻገር በርካታ ተጋባዥ መምህራን እየመጡ ያስተምሩ ነበር፡፡ በተለይ ከኤስ. አይ. ኤም እንዛ ጠይቀን እነ ሚ/ር ፖል ቢልስኪ፣ ሚ/ር ኮልማን እና ሚ/ር ቢርን የመሳሰሉ መጽሐፍ ቅዱስን በከፍተኛ ደረጃ የተማሩ ሚሲዮናውያን ሁሉ እየመጡ ያስተምሩ ነበር፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱም አስፈላጊነቱ ታምኖበት ዛሬም ድረስ አገልግሎት እየሰጠ እና እያደገ ብዙ አገልጋዮችን ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ማፍራቱን ቀጥሏል፡፡

በጊዜውም ትምህርት ቤቱ በርካታ አገልጋዮችን ለጌጃም ሆነ ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ማፍራት የቻለ ሲሆን ብዙ ትልቅ ስም ያላቸው አገልጋዮችም ይማሩ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሊቀ መንበር እና ምክትል ዋና ጸሐፊ ሆነው ያገለገሉት አቶ ደምሴ ማዴ ሳይቀሩ የተማሩ ሲሆን፣ አቶ አባይ የሚባል አንድ የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ትልቅ አገልጋይም ከመጀመሪዎቹ ተማሪዎቻችን መካከል አንዱ ነበር፡፡ አቶ አባይ ተማሪ በነበረበት ወቅት አንድም ጥያቄ ሳይሳሳት

(ኤክስ ሳያገኝ) በሁሉም ትምህርት መቶ ከመቶ እያገኘ በትጋት ተምሮ ያጠናቀቀ የማዕረግ ተማሪ እንደነበር አስታውሳለሁ።

እኔ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የመክፈት እና ተተኪ አገልጋዮችን የማዘጋጀት እቅዴ ተሳክቶ ትምህርቱ በመጀመሩ ብደሰትም ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ነገ እኔ የማገለግላትን ቤተ ክርስቲያን ሊረከቡ የሚችሉ የበለጠ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ዕጩ አገልጋዮችን ለማዘጋጀት በቅርበት መያዝ እንደሚገባኝ አምኜ ነበር። ስለሆነም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከሆኑት የቤተ ክርስቲያናችን አባላት መካከል አምስቱን ሰዎች መርጬ ከዋናው ትምህርት በተጨማሪ በየዕለቱ ከ10-12 ሰዓት ለብቻቸው አስተምራቸው ነበር። እነዚህ አምስት ተማሪዎቼ ሚካኤል ደንባው፣ ሽፈራው ፈይሳ፣ ታደሰ ኤቢሳ፣ ሞገስ ታደሰና የኋላ እሸት ነበሩ። እነዚህ ያኔ በጣም ወጣት የነበሩ ትንንሽ ልጆች ቢሆኑም ነገ የእኔን የአገልግሎት ቀንበር ይሸከማሉ ብዬ የያዝኳቸው ነበሩ። ዛሬ እነዚህ ሁሉ በያሉበት ታላላቅ አገልጋዮች ሆነዋል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤታችን እየተጠናከረ ሲሄድ እና ተፈላጊነቱ ሲጨምርም መስፈርቶችን አዘጋጅተን መቀበል የጀመርን ሲሆን የምንቀበላቸውን ተማሪዎች ቁጥር በመወሰን በጊዜው 40 ተማሪዎች ብቻ በአንድ ጊዜ የምንቀበል ሲሆን 20 ተማሪዎችን ከኛ ቤተ ክርስቲያን ቀሪዎቹን 20 ተማሪዎች ደግሞ ከሌሎች ቤተ ክርስቲያናት እንዲሆኑ ኮታ አዘጋጅተን ነበር። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከብዙ ቤተ ክርስቲያናት አገልጋዮች እየመጡ ይማሩ ስለነበረ ከሙሉ ወንጌል በብዛት፣ ከገነት፣ ከመሠረተ ክርስቶስ እና ከሌሎችም በርካታ ቤተ ክርስቲያናት አገልጋዮችን ተቀብለን አስተምረናል።

ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አገልጋዮችን ተቀብለን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እናስተምር በነበረበት ጊዜ አንድ አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር። በዚያ ዘመን ቤተ ክርስቲያናችን ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አገልጋዮች እድል ለመስጠት በወሰነችው መሠረት ከልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት የሚመጡ ተማሪዎችን በታላቅ ደስታ እንቀበል ነበር። እኔም እግዚአብሔር አስቀድሞ ተናግሮኝ ስለነበር ከየትኛውም አብያተ ክርስቲያናት የሚመጡትን ለማስተማር ሁልጊዜ ፈቃደኛ ነበርኩ።

እግዚአብሔር እኔ ሌሎችን ተቀብዬ ቃሉን እንዳስተምር የተናገረኝ ገና በቢቾ እያለሁ ሆሳዕና ከተማ እየተመላለስኩ በማስተምርበት ጊዜ ነበር። በዚያ ዘመን በርካታ ሰዎች ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሳይቀር እየመጡ ወንጌልን ይማሩ እንደነበር ተርኬላችኋለሁ።

በዚህ ሁኔታ ሁሉን እየተቀበልኩና እያስተማርኩ እያለ አንድ ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ወደ ሆሳዕና የመጣ በሙያው ድሬሰር የሆነ ሰው ከኛ ጋር መማር እና ማምለክ ጀምሮ ነበር። በኋላ ግን ከኛ ጋር የሚያመልኩ አንዳንድ ተማሪዎችን ለይቶ ይዞ መውጣት (ከኛ መለየት) ጀመረ። እኔም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሙሉ ወንጌሎች ምን እንደሚያምኑ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማንነት፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ

ለና ስለ አጠቃቀሙ በደንብ ተምሬ ስለነበር የእነርሱን አስተምህሮ በሚቃረን መልኩ የመቃወሚያ ትምህርት ማዘጋጀት ጀምሬ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንዳልቀጥልበት ከለከለኝና ዝም ብዬ እንዳስተምራቸው ተናገረኝ።

ጌጃ መጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ቤት አገልግሎት መስጠት በጀመረችበት በዚያ ዘመን የሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተ ክርስቲያን አስቀድማ ተዘግታ ስለነበር ብዙ ተማሪዎች (ዛሬ ትልልቅ አገልጋዮች የሆኑ ሳይቀሩ) በብዛት እየመጡ በደስታ ይማሩ ነበር። ከተወሰነ ጊዜ በኋላም ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን የወጡ የአርነት ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሆኑት እነ ፓ/ር የማነ ብርሃን ለመማር ወደ እኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መጡ። እኛም ተቀበልናቸው። በዚህ ጊዜም ሙሉ ወንጌሎች "እነርሱን ከተቀበላችሁ እኛ እንወጣለን" ብለው ጥያቄ አቀረቡልኝ። በዚህ ጊዜ እኔ በነገሩ አሰብኩበት እና የሙሉ ወንጌል አገልጋዮች የሆኑትን ሰብስቤ ወደ ራሴ ቢሮ በመውሰድ ልዩ ልዩ ጥያቄ አቀረብኩላቸው።

"እናንተ የምትኖሩት ለራሳችሁ ነው ወይስ ለእግዚአብሔር?" ስላቸው እነርሱም "ለእግዚአብሔር ነው የምንኖረው" አሉ።

"እነርሱ ከእናንተ ተለይተው በሄዱበት እንዲጠፉ ነው ወይስ በእምነታቸው እንዲያድጉ?"

"እንዲያድጉ እንፈልጋለን" አሉኝ።

"እነዚህ ሰዎች በእምነታቸው የተነሳ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር ናቸው? ወይስ ወደ ቄራ (ለእርድ እንደተወሰደ ከብት) ወርደዋል?"

"ከእግዚአብሔር ጋር ናቸው።"

ይህን ጊዜ እኔም "እናንተ የእግዚአብሔርን ሥራ መቃወም የለባችሁም። እግዚአብሔር የተቦረቦሩትን አንጾ፣ ገንብቶ ቢያመጣ ምን ችግር አለ?" አልኳቸው። እነርሱም ከስሜታዊነት ረግበው ነገሩን ተቀብለው ዝም ብለው፤ ትምህርታቸውንም ቀጠሉ። እግዚአብሔርም እነርሱንና ሌሎችንም እያስተማርን ወደ ፊት ቤተ ክርስቲያናት ሲከፈቱ እና ሲበዙ የሚያገለግሉ ብዙ አገልጋዮችን እንድናዘጋጅ ተጠቀመብን። ስሙ ብሩክ ይሁን!

# ምዕራፍ ፳፩

# የጠላት ማስፈራራት እና የእግዚአብሔር ጥበቃ ለቤተ ክርስቲያን

## እግዚአብሔር የለም!?

*የ1967 ዓ.ም አብዮት ያመጣው የፖለቲካ ትኩሳት አገሪቱን እያመሰ የወጣቱን ሕይወት እየቀጠፈ እና ከገጠር እስከ ከተማ ጦርነት ተንሰራፍቶ መንግስት ከውስጥ እና ከውጪ ኃይሎች ጋር መዛሪያ ተማገዞ ውጊያ እየተካሄደ ዓመታቱ ይነጉዱ ነበር። የአገሪቱ የቀድሞ መንግስት ከፍተኛ ባለሥልጣናት፣ በልዩ ልዩ ፖርቲዎች ውስጥ ታቅፈው የተንቀሳቀሱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እና ወጣቶች፣ አንዳንድ የኃይማኖት አባቶች እና የተከበሩ ሰዎች ሳይቀሩ ካላቸው የአመለካከት ልዩነት የተነሳ እየተገደሉ አብዮታዊ እርምጃ መወሰዱ ለሕዝብ ይታወጅ ነበር። በአገሪቱ ሞት ርካሽ ነገር ሆኖ ቆየ። በዚህ ዓይነት ሥልጣን የያዘው ወታደራዊ መንግስት ራሱን አጠናክሮ የሶሻሊስት ሥርዓት የሚከተል ብቸኛ ፓርቲ ሆኖ ራሱን አስተዋወቀ። በዚህም ለብዙ ክፍለ ዘመናት ስሙ በተጠራባት እና በተመለከባት አገር በቅዱስ ቃሉ እጆቿን ወደ እርሱ እንደምትዘረጋ የተሰፋ ቃል በተጻፈላት ምድር እግዚአብሔር የለም ተብሎ በይፋ ታወጀ። በየቦታው ቤተ ክርስቲያናት እየተዘጉ ወደ የቀበሌ መሰብሰብያ አዳራሽነት ተቀይረው እግዚአብሔር አድሃሪያን ጭቁኑን ሕዝብ ለመግዛት እንዲያመቻቸው የፈጠሩት ሃሳባዊ ማደናገሪያ እንጂ በእውን የሌላ መሆኑ የሚፈክርባቸው መድረኮች ሆኑ።*

*በዚሁ ጊዜ የአዲስ አበባዋ ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም አብዮቱ ከመፈንዳቱ በፊት የነበራት አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ምዕመናን ላይ ያመኑት በየጊዜው እየተጨመሩ በፍጥነት እያደገች ያለች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሆናለች። በውስጧ ያለው የመንፈስ አንድነትም ጠንካራ አባላት በልዩ ልዩ አገልግሎት ዘርፍ የሚተጉባት ቦታም ነበረች። ከዚህም ባሻገር በየጊዜው ከሚዘጉ ቤተ ክርስቲያናት ለአምልኮ በሚፈልሱ ክርስቲያን ወገኖች፣ ከተለያዩ ሰፈራዎች በተሰበሰቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪዎችና የልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያናት አገልጋዮች የመንፈሳዊ*

ትምህርት መማሪያ ማዕከል ሆናለች። ይህንን ፍሬያማነት ያየ ጠላትም በዚህች አጥቢያ ላይ ጣቱን መቀሰሩ እና የማስፈራሪያ ዛቻውን መሰንዘሩ አልቀረም። ስለሆነም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች እና አገልጋዮች ዘመኑን እየመረመሩ እና ሁኔታዎችን በአንክሮ እየተከታተሉ አገልግሎታቸውን ቀጥለዋል።

ቤተ ክርስቲያኒቱ በዚሁ ሁኔታ ውስጥ እያለችም እንደተለመደው በ1972 ዓ.ም ዓመታዊ የኮንፍራንስ እና የትምህርት ጊዜ አዘጋጀች። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለዚሁ ኮንፍራንስ የሚሆን ትምህርት በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ላይ እንዲያዘጋጁ ሁለት ወራት ያህል ቀደም ብለው ለወንጌላዊ ኬዳሞ አሳወቁ። ወንጌላዊውም በተነገራቸው መሠረት የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍን ለማስተማር ይዘጋጁ ጀመር።

ይሁንና በጉዳዩ ላይ ጊዜ ወስደው ደጋግመው ቢጸልዩም ከተነገራቸው የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ የሚወጣ መልእክት ሊያገኙ ባለመቻላቸው እስከዛሬ በብዙ ስፍራና አጋጣሚ አስፈላጊውን መልእክት እየሰጠ ብዙ ፍሬ እንዲያፈሩ ያደረጋቸውን መንፈስ ቅዱስ በጸሎት ይጠይቁ ጀመር። የእግዚአብሔር መንፈስም በጊዜው ከነበረው ሁኔታ አንጻር ለሕዝቡ ሊያስተላልፍ የወደደውን መልእክት ከዘካሪያስ መጽሐፍ ላይ በመስጠት ይህንኑም በኮንፍራንሱ ላይ እንዲያስተምሩ ተናገራቸው።

ወዲያውኑ ወንጌላዊው ሃሳቡን ለሽማግሌዎች ጉባኤ አቀረቡ። "እናንተ ከዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ትምህርት እንዳዘጋጅ ነግራችሁኝ ነበር። ነገር ግን አሁን ባለንበት ጊዜ እና ሁኔታ ትምህርት ብቻ ሳይሆን መልእክትም ያስፈልጋል። እኔ እንደተነገረኝ በዮሐንስ ራእይ ላይ መልእክት ለማዘጋጀት ብሞክርም አልቻልኩም። ዝም ብሎ ትምህርት ማስተማር ቢቻልም ወቅታዊ መልእክት ግን የግድ ያስፈልጋል። እኔ ደግሞ ለጊዜው የሚሆን ትምህርት እና መልእክት ከዘካሪያስ መጽሐፍ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ሰጥቶኛል።" አሉ። በዚሁ ጊዜ ይህንን የሰሙት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወንጌላዊው የታዘዙትን ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆኑም ብለው በማሰብ ቅሬታ ተሰምቷቸው ጥያቄ ያነሱ ጀመር። ወንጌላዊ ኬዳሞም አይታዘዝም ብለው ላሰቡት መሪዎች ሀሳባቸውን ያስረዱ ጀመር። "እኔ እኮ በመሪዎች የታዘዘውን ነገር ለመፈጸም ፈቃደኛ ነኝ። እናንተን አከብራለሁ፣ እታዘዛለሁም። ነገር ግን ከእናንተ በላይ እግዚአብሔርን መታዘዝ አይገባኝምን? እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ ይህ ትምህርት እና መልእክት ለሕዝቡ እንዲደርስ ፈልጎ መልእክት ሰጥቶኛል። ይህንኑ እንዳስተምር በትክክል እግዚአብሔር ፈልጓል።" አሉ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ከአቋማቸው ተለሳልሰው ኬዳሞ የተቀበሉትን መልእክት እንዲያስተምሩ ተስማሙ።

በኮንፍራንሱ ዕለትም እግዚአብሔር በዘካሪያስ መጽሐፍ ላይ ካለው ሃሳብ በመነሳት ለሕዝቡ ወቅታዊ መልእክቱን አፈሰሰ። በመጽሐፉ ምዕራፍ አንድ ላይ የተገለጸውን ሃሳብ በማንሳት ኬዳሞ እግዚአብሔር ከኃያላን ሁሉ በላይ ኃያል እንደሆነና በየትኛውም ዘመን የሚነሳ ኃያል ከእርሱ በላይ እንዳልሆነ አስተማሩ። በምዕራፍ 2፡4-5 " .. ኢየሩሳሌም በውስጥዋ ካሉት ሰዎችና እንስሶች ብዛት የተነሣ ቅጥር እንደሌላቸው መንደሮች ሆና ትኖራለች። እኔ በዙሪያዋ የእሳት ቅጥር እሆንላታለሁ፣ በውስጥዋም

*ክብር እሆናለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር።" ብሎ ለእስራኤል እንደ ተናገረ ለጊሻ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም በዙሪያዋ ከነበረው አስፈሪ ሁኔታ እግዚአብሔር ቅጥር እንደሚሆንላት የሰጣቸውን መልእክት አስተላልፉ። በቁጥር ስምንት ላይ እንደተገለጸው "... የሚነካችሁ የዓይኑን ብሌን የሚነካ ነውና" እንደተባለው እግዚአብሔር ለሕዝቡ "እናንተን የሚነካ የእኔን ዓይን ብሌን ይነካል!" ብሎ ተናገረ።*

*በዚህ ጊዜ ኮንፍራንሱን የታደመው ጉባኤ "አሜን" ብሎ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን መልእክት ተቀበለ። የሕዝቡም ልብ በዙሪያው ካለው አስጨናቂ ሁኔታ በእግዚአብሔር ተማምኖ አረፈ።*

## ኣንደ ዓይኑ ብሌን ...

የ1970ዎቹ መጀመሪያ በግለሰብም ሆነ በማኅበር ደረጃ ሰው በፍርኃት እየተመላለሰ ነበር ቀናት ቀናትን የሚተኩት። እኔም እግዚአብሔርን በመታመን ወጥቼ እየገባሁ በብዙ ትጋት እና ደስታ ማገልገሌን ብቀጥልም የምናየው እና የምንሰማው ነገር እያሰጋን መሄዳችን ግን አልቀረም። ሰዎች ሲገደሉና ቤተ ክርስቲያናት ሲዘጉ ስናይ አንድ ቀን ነገሩ በኛም ላይ ሊደርስ ይችላል ብለን እንሰጋ ነበር። እግዚአብሔርም ይህንኑ ሁኔታችንን አይቶ እንደ ዓይኑ ብሌን እንደሚጠብቀን የተናገረን ቢሆንም ሁኔታው ግን በየጊዜው አስፈሪ እየሆነ ይሄድ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጥቂት ከቆየን በኋላም በ1973 ዓ.ም አንድ ቅዳሜ ቀን ነገሩ ከፍቶ ከጫፍ ደረሰ። በዚያ ጊዜ በየቦታው አድራጊ ፈጣሪ አዛዥ ሆነው አገሩን ሁሉ የሚያሸብሩት የቀበሌ ሊቀ መንበሮች ነበሩ። በኛ ቀበሌ ሊቀ መንበር የነበረው ሰው ጥበቡ የሚባል ሲሆን የኛን ቤተ ክርስቲያን ለመዝጋትም ሆነ ለመውረስ ብዙም ፍላጎት አልነበረውም። ነገር ግን የእርሱ ምክትል የነበረው ግለሰብ ቤተ ክርስቲያናችንንም ሆነ በውስጧ ያለውን ትምህርት ቤት በመውረስ ያለንን ንብረት የቀበሌ መገልገያ ለማድረግ ከፍተኛ መሻት ስለነበረው ትምህርት ቤቱንም ሆነ ቤተ ክርስቲያኑ እንዲወረስ የአካባቢውን ሕዝብሲ ያሳድም ቆይቶ በመጨረሻ ተሳካለት እና ቤተ ክርስቲያኒቱን ሊወርሱ መንቀሳቀስ ጀመሩ። አንድ ቅዳሜ ቀንም የቀበሌ አመራሮች አብዮት ጠባቂ ወታደሮችን አስከትለው መጥተው በቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ በቀለም መፈክር ይጽፉ ጀመር።

"ርካሽ ባህርይ አይኖርም!"

"አድሃሪያን ይወድማሉ!" የመሳሰሉና ብዙ እኛን ያሸማቅቃሉ ብለው ያሰቧቸውን በርካታ መፈክሮች ጻፉ። እኛም የነበረው ሁኔታ አስግቶን በየጊዜው በቤተ ክርስቲያን እየተሰባሰብን እንጸልይ ስለነበር ወታደሮቹ እና የቀበሌ ሰዎች በመጡ ጊዜ ከሽማግሌዎች ጋር እኔ ቢሮ ውስጥ ተሰብስበን ነበር። እነርሱ መፈክር ሲጽፉ እያየንም ምንም ተቃውሞ አላሰማንም። በዚያ ጊዜ ገና ወጣት የነበረው ሚካኤል ደንባው ተበሳጭቶ "ለምን ትጽፋላችሁ?" ብሎ የሚጽፉትን ሰዎች እጃቸውን በመያዙ እርሱን

ብቻ ወስደው ሲያስሩት ሌሎቻችን ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰጠንን የተስፋ ቃል እያሰብን ተሰብስበን ከጸለይን በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን አባላት በሙሉ እየደወልን እንዲጸልዩ ነግረን ወደየቤታችን ሄድን፡፡ ያቺን ቅዳሜ ማታ እኔም ወደ ቤቴ ሄጄ ከባለቤቴ ጋር ምሽቱን በኃይል ስንጸልይ ቆየን፡፡ እየጸለይን እያለም እኔ የጌጃ መሪዎችን በልዩ ልዩ የመንግስት ኃላፊነት ላይ ትልልቅ ሥራ የሚሠሩ ሆነው ሳለ እግዚአብሔርን ወደው ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ ደፋ ቀና እያሉ ይህ ክፉ ነገር ማጋጠሙ መሆኑ በጣም አሳሰበኝ፡፡ ሕዝቡም በሙሉ ጌታን ወደ ራሱን ሰጥቶ እያመለከ እግዚአብሔር እንዴት ቤተ ክርስቲያን እንድትዘጋ ይፈቅዳል? ብዬ "እግዚአብሔር ሆይ የጌጃ ቃለ ሕይወት ሕዝብ አንተን ምን በደለ? እንዴት ቤተ ክርስቲያን እንዲወስድብን ትፈቅዳለህ? እነርሱ በሙሉ ያንተ ናቸው! አንተ ግፈኛ ነህን?" እያልኩ ምሬት የተሞላበት ጸሎት ስጸልይ እግዚአብሔር አዕምሮዬን የሚያሳርፍ መልስ ሰጠኝ፡፡

በእርግጥ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሕዝብ በዚያ ወቅት የእግዚአብሔርን ቃል ለመማርና በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፎች ላይ ተሰማርቶ ለማገልገል ሁለንተናውን የሰጠ ሕዝብ ነበር፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎችም አርቆ አሳቢዎች እና በብዙ አቅጣጫ ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ የሚጥሩ በሳል አገልጋዮች ነበሩ፡፡ ከዚህ የቤተ ክርስቲያን መዘጋት ስጋት ጋር በተያያዘም እኔና አብሮኝ የሚያገለግለውን ሽመልስ ወዳጆን ሳይቀር አንድ ቀን "ቤተ ክርስቲያን ልትዘጋ ትችላለች እና እናንተ ለወደፊት እንዳትቸገሩ ምን ልትሠሩ ትችላላችሁ? መኪና ወይም ለንግድ ሥራ የሚሆን ነገር ምን እንግዛላችሁ?" ብለው ጠይቀውን ነበር፡፡ እኔም በወቅቱ በነገሩ ቅር ተሰኝቼ "ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ ትኖራለች፡፡ ጸሎት ቤት ሊዘጋ ይችላል፤ ወንጌል ግን አይቆምም፤ እኛም በየቤቱ እየሄድን ወንጌልን እናስተምራለን፡፡ እኛም ልንታሠር እንችላለን፤ ብንታሠርም በእስር ቤት ወንጌል እንሰብካለን፡፡" አልኳቸው፡፡ እነርሱም ቤተሰብ እንዳይቸገር ነገሩን እንዳሰቡበት ገልጸውልን ልንሠራ የሚገባውን እንድናስብበት ነገረውን ነበር፡፡ በኋላም በነገሩ ዙሪያ አሰብንበት እና ከባለቤቴ ጋር ተማክረን ከቤተ ክርስቲያን 1000 ብር ተሰጥቶን የራሳችንን ገንዘብ ጨምረን የውጭ ከብቶች ገዝተን በቤታችን ማርባት ጀመርን፡፡

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ቅዳሜን የጌጃ ሰው በሙሉ በየቤቱ ሲጸልይ አደረ፡፡ እኔም ሌሊቱን አሳልፌ ከጉጉት የተነሳ በ11፡00 ሰዓት ገና ሰማይ እና ምድር ሳይላቀቅ ተነስቼ ወደ ጌጃ በእግሬ አመራሁ፡፡ ልክ በ12፡00 ሰዓት ጌጃ መሠረተ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ስደርስ ሽመልስ ወዳጆ እና አቶ ብርሃኑ ደረሰ ተከታትለው መጡ፡፡

እኛ እዚያው እያለንም የቀበሌው ምክትል ሊቀ መንበር ሰባት ወታደሮች አስከትሎ መጥቶ እንደገና ግቢው ውስጥ መፈክር መጻፍ ጀመሩ፡፡ እኛም ምንም አልተናገርንም፡፡ 'እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን "እኔ የእሳት ቅጥር እሆናታለሁ፡፡ እርሷን የነካ የዓይኔን ብሌን እንደ ነካ ነው፡፡ እንደ ዓይኔ ብሌን እጠብቃታለሁ፡፡" ብሎናልና እርሱ

ቃሉን ያከብራል፤' ብለን የሚያደርጉትን አይተን እንዳላየን ሆነን ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ምድር ቤት ሄደን መጸለይ ጀመርን። ወደ እኛ እየቀረበ መጥቶ ግቢያችን የገባውን አስጊ ሁኔታ ወደ ጌታ እያቀረብን በእምባ ጸለይን። ሕዝቡም ሁኔታውን ለማየት እየመጣ ሰዓት እየረፈደ ሲሄድ የሰዉ ቁጥር ይጨምር ጀመር። ጸሎታችንንም እየጸለይን ቆየን። በጸሎት ላይ እያለንም ከትንቢተ ዘካሪያስ መጽሐፍ ምዕራፍ 8 ላይ *"ስለ ጽዮን ታላቅ ቅንዓት ቀንቻለሁ .... በታላቅም ቁጣ ስለ እርሷ ቀንቻለሁ ... "* የሚለውን ክፍል ሳነብ ሕዝቡ በታላቅ ድምጽ "አሜን!" ብሎ ጮኸ። ያቺ ዕለት በጣም አስደናቂ የጸሎት ቀን ነበረች። በዚያች ዕለት በነበረው ጸሎት 15 ሰዎች ጌታን ተቀብለው አመኑ። ነገሩ ለእኛም ጭምር ከፍርኃት ይልቅ መደነቅ የሞላበት ነበር። በኋላም እግዚአብሔር አስደናቂ ሥራውን ቅጥር ግቢያችን ውስጥ በነበሩት የቀበሌ ሰዎች መካከል ይሠራ ጀመር።

ለሰዓታት በተካሄደው የምልጃ ጸሎት ላይ "እግዚአብሔር ለጌጃ መሠረተ ሕይወት ቀንቻለሁ ይላል፤ ይህ ስፍራ እንደገና የአገልግሎት ቦታ ይሆናል።" ብሏል ስል ሕዝቡ እንደገና "አሜን!" ብሎ በታላቅ ድምጽ ተስማማ። ጸሎታችንን ጨርሰን ስንወጣ በወታደር ተወርሮ የነበረው ግቢያችን ባዶ ነበር። እኛም ምን እንደተፈጠረ ሳናውቅ ቆየን። በኋላም አንዲት ልጇ በእኛ ቤተ ክርስቲያን የምታመልክ ሴትዮ "የእናንተ አምላክ የእውነት አምላክ ነው። ውደዱት፤ አክብሩት፤ እናንተ የሆነውን አታውቁም፤ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ እኮ ነው ቤተ ክርስቲያናችሁ ከመወረስ የተረፈችው።" ብላ መሰከረችልን።

ለካስ እኛ በጸሎት ላይ እያለን እግዚአብሔር የወራሾቻችንን ሃሳብ ደበላልቆት የቀበሌ ሊቀ መንበር እና ምክትሉ በሚወረሰው የእኛ ቤተ ክርስቲያን ንብረት ዙሪያ ሲከራከሩ ቆይተዋል። በኋላም የሁለቱ ሙግት ድብልቅልቅ ወዳለ ጸብ አምርቶ ሲጎዳዱ ሲደርሱ ቤተ ክርስቲያን ሊዘጉ እና እኛን ሊይዙ የመጡ ወታደሮች ሁለቱን ይዘው ወደ መጡበት ተመልሰዋል። እግዚአብሔር ተዓምራት ሠርቶ ቤተ ክርስቲያናችንን ከመዘጋት ታደጋት። ከዚያ በኋላም ማንም ተመልሶ ወደ እኛ አልመጣም። እንደሰጠን የተስፋ ቃልም እግዚአብሔር ለጌጃ የእሳት ቅጥር ሆኖአት፤ እንደ ዓይኑ ብሌን ጠብቋትም የተናገረውን ፈጸመ። እግዚአብሔር በእውነት ታማኝ አምላክ ነው።

በኋላም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተረባርበው ወደ የተለያዩ የመንግስት ቢሮዎች እና ወደ ሌሎች በርካታ ስፍራዎች ደብዳቤ ተብትኖ ቤተ ክርስቲያንም ከስጋት ነጻ ሆና በዚያ ክፉ ዘመን የወንጌሉን ብርሃን በድምቀት ማብራቷን ቀጠለች።

ይሁንና እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ከመዝጋት በማትረፉ ትልቅ ድል ቢሰጠንም ሌሎች ብዙ አስጊ ሁኔታዎች በዙሪያችን አሁንም ማንዣበባቸውን ቀጥለው ነበር። በተለይ በተለያዩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ባለሥልጣን የነበሩ መሪዎቻችን ሁል ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን በታማኝነት ያገለግሉ ነበር። ሳያቋርጡ በቆራጥነት በመስበክ እና በማስተማርም ኃላፊነታቸውን ሁሉ በአግባቡ ይወጡ ነበር። እኛም ከዚህ የተነሳ አንድም ችግር እንዳይገጥማቸው እንጸልይ ስለነበር እግዚአብሔር እንደ ተስፋ ቃሉ

እንደ ዓይነ ብሌን ጠብቆን እንድም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ በመንግስት ሳይወነጀል የስደቱ ዘመን አብቅቷል።

በዚያ ዘመን በወቅቱ የነበረውን የመንግስትን አመለካከት የሚቃወም ስብከት የሰበከ ሁሉ አገር ጥሎ ሸሽቷል። ከኛ ቤተ ክርስቲያን ግን ማንም ሰው ሳይኮበልል ክፉውን ዘመን ተሻግረናል።

እኛ ጋ ግን አንድ ጊዜ አቶ ጥላሁን ኃይሌ ስለ እግዚአብሔር ባለ ሥልጣንነት፣ ኃያልነትና ንጉሥነት ከፍ አድርጎ ሰበከ። በጉባኤያችን ውስጥም ሁል ጊዜ መልእክታችንን የሚቀዱ ካድሬዎች በስውር እንደሚመጡ ስለምናውቅ ከዛሬ ነገ ተይዞ ይጠየቃል ብለን እንሰጋ ነበር። ነገር ግን ማንም ሳይጠይቀው በሰላም ኖረ። እኔም አንድ ቀን ከምሰብከው ስብከት የተነሳ ለጥያቄ እጠራለሁ፤ አንድ ቀን እያዛለሁ ብዬ ብጠብቅም አንድም ቀን ሳልያዝና ሳልጠየቅ ኖርኩ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ወደ ቤተ ክርስቲያናችን የተለያዩ ሰላዮች እንደሚመጡ እና በቴፕ መልእክታችንን እየቀዱ እንደሚወስዱ እናውቅ ነበር። አንድ ጊዜ አንድ የኛ ሀገር ተወላጅ የሆነ ካድሬ አማኝ ነኝ ብሎ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን መጥቶ ለምች ጌታን ሲቀበሉ አብሮ ወጣ። ከዚያ በኋላም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ጊዜ እየቆየ ከቢሮ ቢሮ ዘው ይል ጀመር። ይህ ሰው በፊት የኢ.ህ.አ.ፓ አባል የነበረ በኋላ ደግሞ ወደ ደርግ የዞረ ፖለቲከኛ ነበር።

አንድ ቀን ሰውዬውን ወደ ቢሮዬ ጠራሁት እና ይገባው ገባሁ። ከዚያም "በእውነት አንተ ጌታን ተቀብለሃል?" ብዬ ጠየቅሁት። እርሱም "አዎን" ብሎ ፍርጥም ብሎ መለሰልኝ። እኔም በእውነት ጌታን ካመንክ ትያዛለህ፣ ትታሠራለህ፣ ብዙ ዋጋ ትከፍላለህ። እኔ ደግሞ እንድትታሠር አልፈልግም። ስለዚህ የ12 ሰዓቱን የመጀመሪያ አምልኮ ተካፍለህ ወደ ቤትህ ሂድ። አለዚያ ግን የምትመጣው ለስለላ ከሆነ በኛ ጉባኤ ውስጥ ሁል ጊዜ ከ20 በላይ ሰላይ ይኖራል። አንተ ለምን ትለፋለህ? በእጅ ጽፎ፣ በቴፕ ቀድቶ፣ በሌላም በሌላም መረጃ ሰብስቦ መሄድ አለ። እኛ በስውር የምንሠራው ነገር እንደሌለ ለምን አታውቅም? እኔም ስለ እግዚአብሔር ቃል ለመሞት ዝግጁ ነኝ። ስለዚህ ባትለፋ ይሻላል።" አልኩት። ከዚያ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣቱን ተወ። በመጨረሻ ይህ ሰው ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ታስሮ እንደነበር አስታውሳለሁ።

ያ ዘመን አገር በስጋት የተዋጠበት፣ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ስደት ውስጥ ያለፈችበትና አማኞች መከራ የተቀበሉበት ነበር። እግዚአብሔርም በብዙ የማጽናኛ ቃል በመንፈሱ እየመከረና በተዓምራዊ ጥበቃው እያስደነቀን ቢያበረታንም አስጨናቂው ሁኔታ ግን በተለያየ መንገድ ወደ ቤታችን ሳይቀር ይመጣ ነበር። በዘመኑ ወጣት ባለበት ቤት ሁሉ ጭንቀት አይቀሬ ነበር። የቀይ ሽብር እና ነጭ ሽብር መገዳደል ጋብ ሲል በሱማሌ እና በሰሜን ኢትዮጵያ መካከል ከነበረው ጦርነት የተነሳ ወጣቶችን በግዴታ

ለውትድርና ማፈስ ተጀመረ። ይህም ወጣት ልጆች ያሉንን የቤተ ክርስቲያን አባላት እና መሪዎችን ሁሉ ሳይቀር ሲያስጨንቅ የነበረ ጉዳይ ነው።

ይህ የአፈሳ ስጋት የኛን ቤት በርም አንኳኩቶ ልጄ ሃብተ ወልድ ትምህርት ጨርሶ ስለነበር የቀበሌ አመራሮች ለውትድርና ሊወስዱት ያሳድዱት ነበር። እኛም ለውትድርና ከሄዱት አብዛኛዎቹ የማይመለሱበት ጦርነት ሰለባ እንዳይሆን በማሰብ በጽኑ እንጸልይ ነበር። አንድ ረቡዕ ቀንም ለውትድርና ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ከቀበሌ የመጥሪያ ወረቀት በእጁ ተሰጠው። እኔም ያንን ስመለከት ቤቱ ባለሁበት ጊዜ ስጸልይ ቆይቼ ወደ ቢሮዬ ሄድኩ። ቢሮዬ ከደረስኩ በኋላም ነገሩ አሳስቦኝ እንደገና ተንበርክኬ መጸለይ ጀመርኩ። በእርግጥ እኔ በሕይወቴ በሚሆኑ ወይም ሊመጡ ባሉ ነገሮች ላይ በጣም መጨነቅ አላውቅም። ነገር ግን ሁል ጊዜ በገጠመኝ ነገር ዙሪያ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ እፈልጋለሁ።

እናም በልጄ በሃብተወለድ የውትድርና ጥሪ ጉዳይ መንፈስ ቅዱስ ምን እንደሚል ለማወቅ ጸለይኩ። በኋላም ተነስቼ መጽሐፍ ቅዱሴን ለማንበብ ስከፍት በድንገት የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 7፡1-8 ያለው ክፍል ተገለጠ። በቁጥር አንድ ላይ *"ከዚህም ገኋላ ኢየሱስ አይሁድ ሊገድሉት ይፈልጉ ስለነበር በይሁዳ ሊመላለስ አይወድም ነበርና ገሊላ ይመላለስ ነበር።"* ይላል እኔም በዚህ ክፍል ጌታ ኢየሱስ ራሱን ለአደጋ አሳልፎ እንዳልሰጠ ሁሉ እኔም ልጄን ለአደጋ አሳልፌ መስጠት የለብኝም ብዬ በመወሰን ተነስቼ ወደ ቤቴ ተመለስኩ።

ነዋሪነቷ በአዲስ አበባ የሆነና የደርግ ጀነራል መኮንን ያገባች አንዲት ዘመድ ነበረችኝ። እናም ነገሩ እስከሚረጋጋ ድረስ ሃብተወልድን ወስጄ እነርሱ ቤት ለሦስት ወር ያህል አስቀመጥኩት። በተጨማሪ ወጪ ሰዎቹን እንዳያስቸግርም እኛ ምግብ እንወስድለት ነበር።

የእርሱን አለመኖር ያዩ የቀበሌ ኃላፊዎችም እየመጡ እኔን እና ባለቤቴን በጥያቄ ያዋክቡን ጀመር። እኛም "የመጥሪያ ወረቀቱን የሰጣችሁት ለእርሱ ነው። ይህን ያደረጋችሁትም እርሱ ትልቅ ሰው ነው ብላችሁ ራሱን እንደቻለ አምናችሁ አይደልምን? ራሳችሁ ፈልጉ እና አግኙት። እኛ አላገኘነውም።" እንል ነበር። አንድ ቀን ባለቤቴን ለማስፈራራት ቀበሌ ድረስ ይዘዋት በመሄድ እርምጃ እንወስዳለን ሲሏት "እርሱ ሙሉ ሰው ነው ብላችሁ አይደለም ወይ መጥሪያውን ለራሱ የሰጣችሁት? ራሱን ፈልጋችሁ ለምን አትጠይቁትም? እኛን ለምን ታስጨንቃላችሁ?" ብላ መለሰችላቸው እና ለቀቋት።

እግዚአብሔር ረድቶንም አንድም ልጅ የዚያ ዘመን የፖለቲካ ትርምስ እና የጦርነት እሳት ውስጥ ሳይማገድብን ተሻገርን። በጊዜው ብዙዎች ስደቱን በመፍራት፣ አንዳንዶችም በፖለቲከኞች ማባበል ተታለው ያመኑትን ጌታ በመተው ወደ ኋላ ተመልሰው ከእምነታቸው ተንሸራትተው ታይተዋል። በተለይ እኔ በነበርኩባት የከምባታ እና ሃዲያ ቃለ ሕይወት በቤተ ክርስቲያን በሥልጣን ላይ የነበሩ የቤተ

ክርስቲያን መሪዎች በአብዛኛው ሥልጣን ፈልገው የወጡ እንጂ እግዚአብሔርን ለማገልገል በእውነት የሚፈልጉ አልነበሩም። እነዚህ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን አንቀው ይዘው በትዕቢት ሲኮፈሱ የእውነት ጌታን ሊያገለግሉ የሚፈልጉ ወገኖች በኃዘን ዳር ቆመው ይመለከቱ ነበር። እግዚአብሔርም ያንን ክፉ ዘመን ሲያመጣ እነዚያ እውነተኛ እምነት የሌላቸው በሙሉ ጥርግ ብለው ከቤተ ክርስቲያን በመውጣት ወደ ፖለቲካ ገቡ። ቤተ ክርስቲያንንም ዋጋ ከፍለው ለማገልገል የሚፈልጉ ጥቂት አገልጋይ መሪዎች ተረከቧት።

# ምዕራፍ ፳፪

# ጎጆ እና በቅሎ በአዲስ አበባም ተገኘ

## “ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታዪ አልነገርኩሽምን?”

*ኬዳም እና ቤተሰባቸው አዲስ አበባ ከገቡ አንድ ዓመት ጨርሰው ሁለተኛውን ለመያዝ በመንደርደር ላይ ናቸው። በዚህ ጊዜ ወንጌላዊው ጌሻ አጥቢያ ላይ የጀመሩት የወንጌል አገልግሎት ሰምሮ በነጣው አዝመራ ላይ ሠራተኞች ስለሚያንሱ በትጋት ለማገልገል እና ብዙ ፍሬ ለማፍራት ይባትላሉ። ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ አንዳንድ ዘመዶቻቸው አስቀድመው እንደመከሯቸው እንግዶችን የመቀበል ድካማቸው ተገልጦም ብዙዎች እነርሱን የሚያውቁ ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ የወንጌላዊውን ቤት አጠያይቀው መምጣት እና ማረፍ ጀምረዋል።*

*አንድ ምሽትም እንዲሁ አራት እንግዶች ከናዝሬት እና ወንጂ ከተሞች መጥተው በአዲስ አበባ ጉዳያቸውን ሲፈጸጽሙ ውለው፣ ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ ለአዳር ወደ ወንጌላዊው ቤት አመሩ። ኬዳም በምሽት የተንኳኳውን በር ሲከፍቱ በቤተሰባቸው በጣም የተወደዱ እንግዶች ደጅ ቆመዋል። ግና ምን ይደረግ? በዚያው ዕለት ከሻሸጎ ቀድመው የመጡ ሌሎች አምስት እንግዶች እራታቸውን በልተውና ተጨዋውተው አልጋ ተነጥፎላቸው ተኝተዋል። ጠባቧ የኪራይ ቤት አራቱን ጥቁር እንግዶች እንዴት ታስተናግድ? በዚህ አስፈሪ ምሽት በድንገት የወረደባቸውን የእንግዳ ዱብዳ ለማስተናገድ ወ/ዊ ኬዳም እና ወ/ሮ ታደለች ተፍ ተፍ አሉ። እንግዶቹ እራታቸውን እንዲበሉ ካደረጉ በኋላም ኬዳም ወጣ ብለው የኮንትራት ታክሲ በመጥራት በዚያ ዘመን በጣም ከፍተኛ ዋጋ ሊባል የሚችል 10 ብር ከፍለው አራት ኪሎ አካባቢ ወደሚኖር ሌላ ወንድም ቤት ላኳቸው።*

*እንግዶቻቸውን ካሰናበቱ በኋላ ሰዓቱ በጣም ስለገፋ ኬዳም እና ባለቤታቸው ጎናቸውን ሊያሳርፉ ወደ አልጋቸው ሄዱ። በዚሁ ጊዜ ብዙ እንግዳ በማስተናገድ ሲደክሙ የዋሉት ወ/ሮ ታደለች ወዲያውኑ እንቅልፍ ይዟቸው ጭልጥ አለ። ኬዳም ግን እንግዶቻቸውን በቦታ ጥበት ወደ ሌላ ቤት መላካቸው ከንክኗቸው ሰውነታቸው ቢደክምም አዕምሮአቸው ግን ሰልቶ ዓይናቸው ሳይከደን ያስቡ ጀመር። እንቅልፉም*

*በንና ጠፉ። ያሉበትን ሁኔታ እያወጡ እያወረዱ ሲያስቡ ቆዩና፡ "እዚህ ከተማ ብዙ ሰው የራሱ እና አልፎ ተርፎ የሚያከራየው ቤትና ለመንጓጓዣም የሚጠቀምበት የራሱ መኪና አለው። እኛ ግን እዚህ በኪራይ ቤት ተጣበበናል። እንግዶች እና ልጆቻችን ተፋፍገው ሳይሆን በደንብ እግራቸውን ዘርግተው ሊቀመጡና ሊተኙ የሚችሉበትን ማረፊያ ቤት እግዚአብሔር ለእኛስ ለምን አይሰጠንም? እኔስ ለማስተማርና ለጉብኝት እሩቅ ቦታ ሄጄ እስከ አራት ሰዓት አምሽቼ ተዝናንቼ አስተምሬ የምመለስበት መኪናስ ለምን አይሰጠኝም? " አሉ።*

*ወንጌላዊው ይህንን እያሰቡ "ለምን? ለምን?" ሲሉ፤ መንፈስ ቅዱስ "ጸልይ!' የሚል መልእክት ወደ ልቦናቸው አመጣ። "እውነት ልጸልይ?' አሉና ኬዳሞ ከአልጋ ወርደው በመንበርከክ በዚሁ ርዕስ ላይ መጸለይ ጀመሩ። በጸሎት ላይ እያሉም ራእይ ያዩ ጀመር። "አንድ ትልቅ ተሠርቶ ያላለቀ ሰፊ ሳሎን ያለው ባለ ሦስት መኝታ ቪላ ቤት ..." ታያቸው። በታውም ከመካኒሳ እስከ ጎፋ ሰፈር አቅራቢያ ባለው አካባቢ ነበር። ወንጌላዊው ይህንን ራእይ ካዩ በኋላ ስለ ቤቱም ሆነ ስለ መኪናው ጸልየው ወደ አልጋቸው ተመለሱ።*

*ኬዳሞ ይህንኑ ጉዳይ ለባለቤታቸው ሳያማክሩ ለሃያ ቀናት ያህል በግላቸው ሲጸልዩ ከቆዩ በኋላ ተስማምተው በጋራ ለመጸለይ በማሰብ ጉዳዩን ለባለቤታቸው አሳወቁ። ይሁንና ወ/ሮ ታደለች ነገሩን ሲሰሙ "አይ እኛ አሁን የሚያስፈልገን ቤት ነው!' ብለው ጠንከር አድርገው በኃይለ ቃል ተናገሩ። ኬዳሞም መንፈስ ቅዱስ ለሁለቱም ጸልይ ብሎኛል ቢሉም ሰሚ አላገኙም። በመጨረሻም ተሸንፈው ባልና ሚስቱ በመስማማት ስለ ቤት ብቻ ይጸልዩ ጀመር።*

---------------------//--------------------

ይህ ክስተት የተፈጠረው ነሐሴ 1967 ዓ.ም ላይ ነበር። እኔና ታደለች አብረን ስለቤት ስንጸልይ ቆየን። በዚሁ ሁኔታ ላይ እያለንም ከእለታት በአንዱ ቀን የቤተ ክርስቲያናችን አባል የሆነው ካፒቴን ዮሐንስ እና ባለቤቱ ሊጎበኙን ወደ እኛ ቤት መጡ። ቀደም ሲል እኛ በ50 ብር ተከራይተን ወደምንኖርበት ቤት ከገባን በኋላ ቤቱን መንግስት ወርሶት ኪራዩ ተቀንሶልን ለቀበሌ 25 ብር እየከፈልን ነበር የምንኖረው። ቤቱ ከማነሱ በስተቀር በጣም ጥሩ እና ለጌጃ ቅርብ የሆነ ቦታ ላይ የሚገኝ ነበር። ካፒቴን ዮሐንስም ቤታችንን ካየ በኋላ "ግቢያችሁ ሰፊ ስለሆነ ቤቱን አስፍታችሁ እዚሁ እንድትሠሩ ከቀበሌ ፈቃድ አውጡ፤ ገንዘቡን እግዚአብሔር ይሰጣችኋል።" ብሎ መከረን። እኔም ይህ የጸሎት መልስ ነው፤ ስለ ቤት እየጸለይን ነው አልኩት። ይህንን ያልኩት ላስቀይመው ስላልፈለግሁ ነበር። ስለዚህም ቀበሌ ሄጄ ቤት እንድሠራ እንዲፈቅዱልኝ ጠየቅሁ።

የቀበሌው ምላሽ ግን አይሆንም የሚል ነበር። "አይሆንም አልክ" አልኩት አይሆንም ያለኝን ሰው። "አዎ" አለኝ። በቃ እሺ ብዬ እባካችሁ ፍቀዱልኝ ብዬ ደግሜ ሳልጠይቅ

ወደ ቤቱ ተመለስኩ። ይህ የቀበሌው እምቢታ ለኔም እግዚአብሔር ያሳየኝን ቤት እንደምናገኝ በቂ መልስ ነበር።

በኋላም ለካፒቴን ዮሐንስ ቀበሌዎች አንፈቅድም ብለዋል ካልኩት በኋላ እግዚአብሔር ያሳየኝን ራእይ እና የጸሎት ርዕስ ጨምሬ ስነግረው እጅግ ደስ አለው። ከዚህ በኋላ ጸሎታችንን ቀጥለን ቆየን።

በ1970 ዓ.ም በባንክ 1500 ብር ብቻ ነበረኝ። ይህንን ብር ማጠራቀም የቻልኩት ከደመወዜ ላይ በወር 60 ብር ያህል እንቆጥብ ስለነበር ነው። በመጀመሪያ ከመንግስት 500 ካ.ሜ ቦታ በነጻ ይሰጥ ስለነበር እንደዚያ የሚሰጠውን ቦታ 30 ብር ከፍዬ ወስጄ በዚያ ላይ ዛኒጋባ ቤት እቀልሳለሁ፤ ቤቱን ለመሥራትም 3000 ብር ብቻ ይበቃል ብዬ አስቤ ነበር። በኋላም እየጸለይንና ከአንዳንድ ቦታም ድጋፍ እየተደረገልን ገንዘቡ 8000 ብር ያህል ደረሰ። በዚህ ጊዜ ለደላሎች የሚሸጥ ቤት እንዲፈልጉልኝ ነገርኩ እና ቤት ያሳዩን ጀመር።

በመጀመሪያ አንድ ያለቀና ጣውላ ሁሉ የገባለት ቤት አሳዩኝ እና "ይህ የኔ ቤት አይደለም፤ የኔ ቤት ያላለቀ ነው" አልኳቸው። በኋላም አንድ ደላላ ወስዶ ያላለቀ ትልቅ ቤት አሳየኝ። እኔም ገና ሳየው "ይህ ቤት የኛ ነው" ብዬ ደመደምኩ። ባለቤቱ ቤቱን ስታየውም በመጀመሪያ "ቤቱ ያው ትልቅ ቤት ነው፤ ነገር ግን ብዙ የሚሠራ ሥራ አለው።" አለች። እኔም "ብር ዘግቼ ማደር ከቻልኩ መዝጊያ ከገባለት ይበቃኛል። ገዝተን ገብተን ቀስ እያልን እንሠራዋለን።" አልኳት። ቤቱ ቫቲካን ኤምባሲ ጀርባ ያለ ስለነበር እኔ በራእይ ካየሁት አካባቢ ጋር እንዲሁም የቤቱ አለማለቅ ሁኔታ ተመሳሳይ ነበርና ልንገዛው ወሰንን።

የቤቱን ባለቤት ዋጋ ስንጠይቀው በመጀመሪያ "16 ሺህ ብር" አለ። በኋላ እኔ 11 ሺህ ብር ሽጥልን። ልል እያሰብኩ እያለ ባለቤቴ ቀድማ "13ሺህ ብር ሽጥልን" ስትል "በዚህ ዋጋ አልሸጥም።" አለ። እኔም "ስማ ይህ ቤት የኛ ቤት ነው፤ እኔ እንደውም 11 ሺህ ልልህ ነበር እርሷ ቀድማኝ ነው 2 ሺህ የጨመረችልህ።" በዚህ ዋጋ ሽጥ አልኩት። እርሱም "አይሆንም" በማለቱ እኛም ትተን ተመለስን። ግን ወዲያውኑ እኛ የምንኖርበት ቤት ግቢ ውስጥ ባለ ስልክ ደውሎ "ኑ ቤቱን ግዙ" አለን። እኛም በዚያ 8,000.00 ብር ላይ ከአገር ቤት ጥጃም ሌላም ነገር ተሸጦ ገንዘብ መጥቶ፤ ከተለያዩ ሰዎችም የተወሰነ ገንዘብ ተበድረን አሟልተን ከፍለን ወደ አዲሱ ቤታችን ገባን።

ስለ መኪና መንፈስ ቅዱስ እንድንጸልይ የተናገረኝን ግን ታደለች እስክታምንበት ድረስ ሳንጸልይ ቆየን። አዲሱ ቤታችን ከጌጃ ራቅ ያለ ስለነበረም ማታ ማታ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አስተምሬ ስጨርስ በ5 ቁጥር አውቶብስ እመለስ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ግን ትምህርቱ ዘግይቶ 2 ሰዓት ካለፈ አውቶብሱ ያመልጠኝ እና በታክሲ ወይም በእግሬ ቤት እገባ ነበር። አንድ ቀን ምሽቱን አስተምሬ ዘግይቼ ከቤተ ክርስቲያን ግቢ ስወጣ አውቶብሱ ቀድሞኝ ስለሄደ ሌላ የምሄድበት አማራጭ አልነበረኝም። ከዚህም በላይ ዝናብ እየዘነበ ነበርና ዝናቡን ተጠልዬ ላሳልፍ ብል በዘመኑ የሰዓት እላፊ ታውጆ

ስለነበር በጣም መሽቶ ውጪ ከማድር ከጌጃ ጀምሮ እስከ ቤቴ ድረስ በዝናብ እየተደበደብኩ ልብሴም እርሶ ሰውነቴም ቀዝቅዞ ቤቴ ገባሁ። ይህንን ያየችው ባለቤቴም "መኪና አያስፈልገንም ብዬ አንተን በዝናብ ያስደበደብኩህ እኔ ነኝ። ጥፋተኛዋ ራሴ ነኝ፤ ከዛሬ ጀምሮ መኪና እንዲሰጠን እጸልያለሁ።" አለችና ጌታ መኪና እንዲሰጠንም ጸሎት ተጀመረ።

አዲሱ ቤታችን ከገባን በኋላም ግቢው ሰፋ ያለ ጥሩ ቤት ቢሆንም አጥር ስላልነበረው ሰው ግቢውን እያቋረጠ በደጃፋችን ነበር የሚተላለፈው። ስለሆነም እግዚአብሔር ገንዘብ እንዲሰጠን ጸልየን ለአጥር የሚሆነንን ገንዘብ ሰጠን። አጥሩ ከታጠረ በኋላም በሩ ባለበት ትይዩ ልክ በሩ በሚከፈትበት ቦታ ላይ የነበረ ትልቅ የባህር ዛፍ ተነቅሎ ጉቶው ቀርቷል። ሁል ጊዜ በራችን ሲከፈት የሚያጋጥመው ያ ጉቶ ስለነበረ ደጃፋችን የነበረውን ውበት ከመቀነሱም ባሻገር ለመጪው እና ሂያጁ እንቅፋት የሆነ ደንቃራ ነበር።

ዓርብ ቀን እኔ ከአገልግሎት የማርፍበት ቀን ስለነበር ባለቤቴን እና ልጆቼን ነገ ጠዋት ጉቶውን እንነቅላለን ብዬ ነግሬያቸው አደርን። በዚያ ዕለት ማለዳ ተነስተንም ባለቤቴ ያዘጋጀችውን ጥሩ ቁርስ በልተን ቡና በቅቤም አዘጋጅታ ስለነበር እርሱን ጠጥተን ወደ ሥራ ገባን። ጠዋት ከ2:30 የጀመርንም እስከ 9:00 ሰዓት ድረስ ታግለን ጉቶው ተነቅሎ ወጣ። የዚህን ጉቶ ታሪክ "የእንቅፋት ጉቶ" በሚል ርዕስ ብዙ ቦታ ስሰብከት ስጠቀምበት ቆይቻለሁ።

---------------------//---------------------

*በ2006 ዓ.ም የዚህ ጽሑፍ አቀናባሪ እና ባለታሪኩ ወንጌላዊ ኬዳም በግንቦት ወር ከዚሁ የታሪክ መጽሐፍ ዝግጅት ሥራ ጋር በተያያዘ ወደ ሻሾን ምድር አምርተዋል። ወንጌላዊው በዚህ የትውልድ መንደራቸው በቢዲቃ ቃለ ሕይወት የተዘጋጀ ኮንፍራንስ ላይ ለመስበክም ነበር በወቅቱ ወደ ስፍራው ያመሩት። ሻሾን፣ ቢዲቃ ቀበሌ ደርሰው ለዘመድ ወዳጅ እና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰላምታ ሰጥተው በምሽት ፕሮግራም ላይም የምክር ቃል አስተላልፈው የትውልድ መንደራቸውን የሚያስጎበኙትን ጸሐፊውን እንግዳቸውን አስከትለው ወደ አንድ ወዳጃቸው ቤት አምርተዋል። በጊዜው ወደዚህ ሰው ቤት ለአዳር የተሄደው ሻሾን ዛሬም ድረስ ካስዋቡአት ጎጆ ቤቶች የተሻለ በከተማ የቤት አሠራር ዓይነት የተሠራ ጥሩ ቤት ያለው እርሱ ስለሆነ ነበር። ይሁንና አካባቢው የኤሌክትሪክ መብራት ስላልነበረው እንግዶቹ በጨለማ ገብተው አድረዋል።*

*እንደልማዳቸው በማለዳ የተነሱት እና ለአገልግሎት በመዘገጃጀት ላይ የነበሩት ኬዳምም የአሳዳሪያቸውን በደንብ የታጠረ ሰፊ ቅጥር ግቢ ዙሪያ ገቡን ተመለከቱ። በዚሁ ግዜ በግቢው ውስጥ አንድ የሻሾን ምድር ሳርን እንደልቡ እየሸረደመ የደለበ ፈረስ ወዲህ እና ወዲያ ሲሯሯጥ አዩና የማን መሆኑን ሲጠይቁ የቤቱ ባለቤት ፈረሱ የእርሱ መሆኑን ሲነግራቸው "ሰው ሁል ጊዜ በእግሩ መሄድ የለበትም። መጓጓዣ በጣም አስፈላጊ ነውና እንኳን ገዛህ። በእግር ሁል ጊዜ ሱክ ሱክ ማለት ጥሩ*

*አይደለም። ውሸም ሁል ጊዜ ሱክ ሱክ ሲል ነው እድሜው ያጠረው" አሉ። የጸሐፉ አቀናባሪን ጨምሮ በአቅራቢያው የነበሩ ሁሉ በነገሩ ተገርመው ሳቁ።*

*ኬዳም ከዚህ ቀደም ገጠር በነበረው ኑሮአቸው (በሻሾንም፣ በጌዲኦም፣ በማረቆም ሆነ በዱራሜ እና ባቢቾ) ወደ ጉዳያቸው የሚሄዱትና ወንጌልን የሚያገለግሉት በፈረስ እና በበቅሎ እየተመላለሱ ነበር ። ሁኔታው ሲያመችም ከራሳቸው አልፈው ለባለቤታቸው ሁሉ በቅሎ ይገዙላቸው ነበር። ወደ አዲስ አበባ ከመጡ በኂላም የከተሜነት ኑሮ እንደሚጠይቀው ፈረስ ልጋልብ ባይሉም የሚያሽከረክሩት መኪና እንደሚያስፈልጋቸው ካመኑበት ግን ቆይተዋል። መንፈስ ቅዱስም በዚሁ ላይ እንዲጸልዩ አሳሰባቸዋል። ባለቤታቸው ወ/ሮ ታደለችም በስተመጨረሻ በጉዳዩ ተስማምተው ቤተሰባቸው ስለ መኪና መጸለይ ጀምሯል።*

--------------------//-------------------

በ1973 ዓ.ም በዝናብ ተደብድቤ ቤት ከገባሁበት ዕለት ጀምሮ እኔና ባለቤቴ ስለ መኪና መጸለይ ቀጥለናል። ይሁንና የመኪናውን መገኘት ፍንጩንም ሳንሰማ ጥቂት ዓመታት አለፉ። እኛም እግዚአብሔር በጊዜው ያመጣዋል ብለን እንጠብቃለን እንጂ ዝግጅት ማድረግ አልጀመርንም ነበር። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለንም 1976 ዓ.ም መጣ። በጊዜው የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ የነበረው አቶ ደምሴ ማዴ ሁል ጊዜ "የመንጃ ፈቃድ አውጣ" ይለኝ ስለነበር እኔም "የራሴ መኪና ከሌለኝ የመንጃ ፈቃድ ምን ያደርግልኛል?" እል ነበር። በጊዜው የነበረችው የቤተ ክርስቲያናችን ኩምቢ ቮልስ ዋገን መኪናንም የሚቆጣጠራት እና የሚነዳት ብዙ ሰው ነበር። ስለዚህ "እኔ መንጃ ፈቃድ አውጥቼ እርሷን መንዳት አልፈልግም፤ ንትርክ ውስጥ ከመግባት አርፌ በታክሲዬ እየተመላለስኩ አገለግላለሁ" እል ነበር።

በመጨረሻም ከአቶ ደምሴ ጭቅጭቅ ለማረፍ ስል ብቻ ሄጄ የጽሑፍ ፈተና ብፈተንም ያገኘሁትን ውጤት ለማየት ግን ሳልሄድ ቀረሁ። በኋላም አቶ ደምሴ እራሱ ሄዶ ማለፌን አይቶ መጥቶ ነገረኝ። ነገር ግን እሁንም እንዲሁ በባዶ መልፋት መስሎኝ ቀጣዩን ትምህርት ለመማር ሳልሄድ ቆየሁ።

አንድ እሁድ ማለዳ በቤተ ክርስቲያናችን አምልኮ ላይ የምትሰብከው ወንጌላዊት ጸሐይ አለሙ የምትባለው የቤተ ክርስቲናችን አገልጋይ ነበረች። በኋላ እርሷ በቀበሌ የሴቶች ስብሰባ ስለነበር ከሰፈር እንዳትወጣ ተከለከለች። ከዚያም አቶ ደምሴ ጋ ደውላ "እኔ ከሰፈር እንዳልወጣ ተከልክያለሁ። ሌላ ሰው እንዲሰብክ አድርግ" አለች። አቶ ደምሴም ወዲያው ተዘጋጅቼ እንድመጣ እና እንድሰብክ እኔ ጋ ደወለ። እኔም "እሺ" ብዬ የምሰብከው ቃል ለማዘጋጀት ጸለይኩ እና ተነስቼ መጽሐፍ ቅዱሴን ስከፍት የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 11 ላይ ያለው ጥቅስ ልክ በትልልቅ ፊደል እንደተጻፈ ቦግ ብሎ ታየኝ። **"ኢየሱስም ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታይ አልነገርኩሽምን?"** አላት ይላል። ወዲያው ጥቅሱ እና ምዕራፉ በሙሉ ለልቤ በራልኝ።

ከዚያም ምንም ዓይነት ጽሑፍ ሳላዘጋጅ ተነስቼ ቀጥ ብዬ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩ። መድረክ ላይ ቆሜም መልእክት ማቅረብ ጀመርኩ። በጥቅሱ ላይ መሠረት አድርጌም "የእግዚአብሔርን ክብር ለማየት ሌላ ምንም አማራጭ የለም ሚያስፈልገው እምነት ብቻ ነው። የሚያምን ሰው የእግዚአብሔርን ክብር ያያል። የእግዚአብሔርን ክብር ከማየት በላይ ደግሞ የሚያረካና የሚያሳርፍ ነገር የለም።" ብዬ ተናገርኩና ሙሉ ምዕራፉ ላይ ያለውን ታሪክ አያይዤ ከምዕራፉ ቁጥር አንድ ጀምሮ ያለውን እያነሳሁ ኢየሱስ አስቀድሞ የአልአዛር ሞት እንዴት የእግዚአብሔርን ክብር እንደሚገልጽ እንደተናገረ፣ እየጠቀስኩ ምንም ጽሑፍ ሳልጠቀም በደንብ ሰበክሁ። በዚሁ ሁኔታ ላይ እያለሁም ገና ስብከቴን ጨርሼ ሳልወርድ እዚያው ቆሜ እያለ መንፈስ ቅዱስ "አንተስ ለምን አታምንም?" አለኝ። "አንተ ብታምን መንጃ ፈቃድም መኪናም ይኖርሃል።" ብሎም አከለ።

ይህን ጊዜ እግዚአብሔር ስላለማመኔ በግልጽ ሲናገረኝ ስለሰማሁት በጣም አለቀስኩ። እዚያው ሆኜም "እሺ አምንሃለሁ።" አልኩትና ወዲያውኑ የመንጃ ፈቃዱን ትምህርት ለመቀጠል ለመሄድ ወሰንኩ።

ሰኞ በጠዋት ተነስቼም አዲስ አበባ ስታዲየም አካባቢ እርሱን መሰናክል ያስተማረውን እንዲያገናኘኝ ከኔ ቀድሞ መንጃ ፈቃድ ካወጣው ልጄ ሀብተ ወልድ ጋር ተያይዤ ሄድኩ። ነገር ግን የሀብተ ወልድ አስተማሪ በዚያ ቀን ሳይመጣ ቀረ። በኋላም አበራ የሚባል ወንድም መጣና ሰላም አለኝ። እኔም ለሰላምታው ምላሽ ከሰጠሁ በኋላ ስላላወቅሁት "ማን ነህ ግን?" አልኩት። እርሱም "ትናንት አንተ ስትሰብክ እኔም እዛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበርኩ" አለኝ። ከዚያም እኔ መኪና አስተማሪ መሆኑን ሳውቅ "ታዲያ እኔን ለምን አታስተምረኝም?" ስለው ግባ ብሎኝ ወደ መኪናው ሄደ።

መኪናው ውስጥ ገብቼ በሹፌሩ ቦታ ቁጭ ብዬም "የመኪናውን ሞተር አስነሳ!" ሲለኝ "የመኪና ቁልፍ የያዝኩት ዛሬ ገና ነው።" አልኩት እርሱም "ትናንት የተሰበከው ስብከት በአንተም ላይ ይሠራል።" አለኝ። እኔም ያው ስብከቱ ንስሃ አስገብቶ መኪና እንድማር እንዳመጣኝ ነገርኩትና ማስተማሩን ጀመረ። ወዲያውኑ የመሰናክል ፈተናውን አስተምሮ አሳለፈኝ። ከዚያም ቀጣዩን የከተማ ትምህርት አንድ ቮልስ ዋገን ያለው ማኅለያ የሚባል ጥሩ ወንድም ስለነበር እርሱ አስተማረኝ። በሁለት ወር ከአስር ቀኔ ትምህርቴን አጠናቅቄ የመንጃ ፈቃድ ተቀበልኩ።

ይህ ታሪክ በ1976 ዓ.ም ተፈጽሞ መንጃ ፈቃዴን አውጥቼ አንዳንድ ጊዜ የጌጃን ኩምቢ ቮልስ እየነዳሁ ቆየሁ። በዚህ ሁኔታ እያለሁም 1977 ዓ.ም መጣ። በአገራችን ከተከሰተው ድርቅ ጋር በተያያዘም ብዙ የውጪ ዕርዳታ ድርጅቶች እንዲገቡ መንግስት ፈቀደ። በጊዜው የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን የልማት ሥራ ሲረዱ የተለያዩ የውጪ ድርጅቶች ወደ አገራችን ይመጡ ጀመር። ዓለም አቀፋዊው የወንጌል አገልጋይ ቢሊ ግራሃም የመሰረቱት የሰማሪታንስ ፐርስ የዕርዳታ ድርጅት ኃላፊዎችም ከረዳዎቹ አንዱ ሆነው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። በዚሁ ጊዜ ወደ አገራችን የመጣው እና የወቅቱ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆነው ፍራንክሊን ግራሃም በቤት

ክርስቲያናችን ዋና ጽሕፈት ቤት ተገኝቶ ከወቅቱ ዋና ጸሓፊ ከነ ዶ/ር ሙላት ጋር የተለያዩ ሥራዎችን አከናወኑ። አንድ ቀን ከዶ/ር ሙላት ጋር ሆነው መጥተው የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን ጎበኙ እና ከእኔ ጋር አብረን ወደ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት በመኪና መሄድ ጀመርን። በጉዞአችን የቢሊ ግራሃም ልጅ የሆነው ፍራንክሊን ግራሃም ከረዳቶቹ ጋር አብሮን ነበር። ልክ በመሄድ ላይ እያለንም መንፈስ ቅዱስ "ለእነዚህ ሰዎች ስለ አንተ የሥራ ጉዳይ ለምን አትናገርም?" አለኝ።

ወዲያውኑም ጉዳዩን ለዶ/ር ሙላት ነገርኳቸው። "ለእነዚህ ሰዎች ስለ እኔ የአገልግሎት ታሪክ እና የመጓጓዣ መኪና እንደሚያስፈልገኝ ለምን አልነግራቸውም?" አልኳቸው። ዶ/ር ሙላትም በሀሳቡ ተስማሙና ፈቀዱልኝ። እኔም ታሪኬን አሳጥሬ እንዲህ ብዬ ነገርኳቸው። "በጌዲኦ፣ በማረቆ፣ በሻሾጎ ... የወንጌል አገልጋይ ሆኜ በእግሬና ከዚያም በኋላ የራሴን በቅሎ እየገዛሁ ሳገለግል ኖሬአለሁ። አሁን በአዲስ አበባ እየተዘዋወርኩ እያገለገልኩ ብዙ ዓመት ሆነኝ። እዚህ ደግሞ መኪና ያስፈልገኛል።" አልኩ። በጊዜው ዶ/ር ሙላቱ እኔ በአማርኛ የምናገረውን በእንግሊዝኛ ያስተረጉሙ ነበር። ፍራንክሊንም ወዲያውኑ "ስለመኪና እንጸልያለን!" የሚል መልስ ሰጠ። እዚያው ባለንበትም "እግዚአብሔር መኪና እንዲሰጣቸው እንጸልይ!" ብሎን ጸለየና ተለያየን።

ይህ ታሪክ ከተፈጸመ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ሰማሪታንስ ፐርሶች ወዲያውኑ "የምትፈልገው ምን ዓይነት መኪና ነው? ዋጋውስ ስንት ነው?" የሚል ጥያቄ በቃለ ሕይወት በኩል ላኩብኝ። እኔም መግዛት የምፈልገውን መኪና ዓይነት ቀድሜ ወስኜ ስለነበር ወዲያውኑ ምላሽ ሰጠሁ። ቀድሞውንም እኔና ባለቤቴ በመንገድ ላይ በእግራችን ስንሄድ ቮልስ ዋገን መኪና ላይ "እኔ እግዚአብሔር ገንዘብ ቢሰጠኝ የምገዛው የዚህች ዓይነት ቮልስ ዋገን መኪና ነው" እል ነበር። ዋጋውንም ለማጣራት ያህል ከደላሎች ስጠይቅ በነገሩኝ መሠረት ዋጋው ከ14 ሺህ እስከ 15 ሺህ ብር እንደሚሆን ነገርኳቸው። እነርሱም 14,900 ብር ላኩልኝ።

ከቤተሰቤ ጋር እግዚአብሔርን አመስግነን በተላከው ገንዘብ (ስለመኪና የሚያውቁትን አቶ ደምሴን፣ ቮልስ ዋገን የነበራቸውን አቶ ላቀውንና እነርሱን የመሳሰሉ ሰዎችን አማክሬ) ጥሩ ይዞታ ያላትን የጀርመን ስሪት ቮልስ ዋገን መኪና በደንብ አስፈትሼ ገዛሁ። ይህቺ ቮልስ ዋገንም ላለፉት ሦስት አስርት ዓመታት ያህል እግዚአብሔር እንደገና ሰማሪታን ፐርስን ተጠቅሞ ሌላ ለከተማም ለክፍለ ሀገርም የሚሆን መኪና እስኪያዘጋጅልኝ ድረስ ያለምንም ችግር የአገልግሎቴ ቁልፍ አጋር ሆና በታማኝነት አገልግላኛለች። እግዚአብሔርም በጌጃ ቃለ ሕይወት መድረክ ላይ "እመን፤ ብታምንስ የእግዚአብሔርን ክብር ታይ ነበር?" ያለኝን ቃል በታማኝነት በራሱ አስደናቂ አጋጣሚ ፈጸመ። እርሱ በቃሉ ታማኝ አምላክ ነውና። የሰማሪታንስ ፐርስ ድርጅትም ለመልካም ዓላማ በታላቅ የወንጌል አገልጋይ የተቋቋመ እንደመሆኑ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የእኔን አገልግሎት የሚደግፍ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋልና እግዚአብሔር ይባርካቸው። ከዚሁ ተቋም ጋር ያለኝ ግንኙነት በዚሁ ሳያበቃም እግዚአብሔር

እንደልማዱ ከብዙ ዓመታት በኋላ በተዓምራት አገናኝቶን ለሌላ በሕይወቴ ለተፈጸመ አስደናቂ ተዓምር ምክንያት ሆኑ። ይኸው ድንቅ ታሪክም በጊዜው በኋለኞቹ ምዕራፎች ላይ ይቀርባል።